333333999933

የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የመንግስት መ/ቤቶች ንብረት አወጋገድን በተመለከተ

የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ረቂቅ ሪፖርት

ጥር 2007 ዓ.ም.

አዲስ አበባ

ማውጫ

ክፍል አንድ 1

መግቢያ 1

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አመሠራረት 1

የአገልግሎቱ ራዕይ 2

የአገልግሎቱ አላማ 2

የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር 2

የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅር 3

የአገልግሎቱ የሰው ሀይል አደረጃጀት 3

የፋይናንስ ምንጭ 4

የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ ጥናት እና የንብረት ዋጋ ግምት ማስወገድ የስራ ሂደት የአሰራር ሥርዓት መግለጫ/Process description/ 4

የኦዲቱ አላማ 5

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ 5

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) 5

የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች 6

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ 7

ክፍል ሁለት 8

የኦዲት ግኝቶች 8

በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት አወጋገድ መመሪያ ስለመኖሩ ፣ ለሚመለከታቸው አካላት ስለመሰራጨቱ ፣ ተግባራዊ ስለመደረጉ እና 8

በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት 8

ወቅታዊ ክለሳ መደረጉን በተመለከተ፤ 8

አገልግሎቱ የሚያስወግዳቸውን ንብረቶች ዝርዝር በመረጃ ቋት /data base/ በመያዝ የሚወገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ በስትራቴጂክና በአመታዊ እቅድ ማስቀመጡንና አፈጻጸሙን መከታተሉን በተመለከተ፤ 10

አገልግሎቱ ንብረት በሚያስግድላቸው መ/ቤቶች የሚወገድ ንብረት መኖሩን ለማረጋገጥ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ ስለመላኩና መልስ ስለመስጠታቸው ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤ 11

በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ... 12

መወገዳቸውን በተመለከተ፤ 12

አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ አገልግሎቱን 27
ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሰው ኃይል ያለው 27
መሆኑን በተመለከተ፤ 27
ለሚወገዱ ንብረቶች የተሰራ ቀመር መኖሩን በተመለከተ፤ 27
አገልግሎቱ ለሚወገዱ ንብረቶች የሚያወጣቸው ጨረታዎች 29
ተሳታፊዎችን ሊደርስ የሚችል መሆኑን በተመለከተ፤ 29
ተጫራቾች ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ከመጫረታቸው በፊት 29
የቀረበውን የጨረታ ሰነድ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የሚያገናዝቡበት 29
በቂ ጊዜ መስጠቱን በተመለከተ፤ 29
የጨረታ አሸናፊ ንብረት ሲረከብ በጨረታ ሰነዱ ላይ በቀረበው 31
ዝርዝር መሰረት መሆኑን በተመለከተ፤ 31
የጨረታ አሸናፊ የሆነ ባለሀብት የሚጠበቅበትን ክፍያ ከፈጸመ በኃላ 32
የሚደረገው የንብረት ርክክብ ወቅታዊ መሆኑን በተመለከተ፤ 32
በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች በጨረታ ያስያዙት ገንዘብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተመላሽ መደረጉን በተመለከተ፤ 34
የአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ ሂደት 35
በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መሆኑን በተመለከተ፤ 35
አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ንብረት ለሚያስወግድላቸው ባለድርሻዎች መደበኛ እና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱን በተመለከተ፤ 36
ክፍል ሦስት 39
የመደምደሚያ ሃሳቦች 39
ክፍል አራት 42
የማሻሻያ ኃሳቦች 42
አባሪ 1 የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች Audit Issues and Evaluative Criterias........ 1

ክፍል አንድ

መግቢያ

የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት አመሠራረት

1. መንግሥት በየዓመቱ ከሚመድበው በጀት ውስጥ እስከ 70 በመቶ የሚደርሰው ለግዥ የሚውል ነው፡፡ የግዥ አፈፃፀም ውጤታማነት የሚለካው ፍላጎትን ለሟሟላት ወጪ ለተደረገ ገንዘብ ተገቢውን ጥቅም ማስገኘት መቻሉ ሲረጋገጥ ነው፡፡ ይሁን እንጂ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከፍተኛ መጠን ያለው የመንግሥት ሀብት የሚፈስበት የመንግሥት ግዥ ተገቢውን ትኩረት ባለማግኘቱ አፈፃፀሙ አዝጋሚና ለብክነት የተጋለጠ ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ለግዢ ሥራ የሚመደቡ ባለሙያዎች በቂ የትምህርት ዝግጅት የሌላቸው እና በልምድ ብቻ የሚሠሩ ነበሩ፡፡

2. ለመንግሥት ግዥ ለተከፈለ ገንዘብ ተመጣጣኝ ጥቅም መገኘቱን ለማረጋገጥም የግዥ አፈፃፀም ሥርዓቱን የበለጠ ሀብትና ጊዜ ቆጣቢ እንዲሁም ግልጽ አሠራርን መሠረት አድርጎ በውድድር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የሚያስችሉ አደረጃጀቶች እንዲኖሩት ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡

3. ንብረት ማስወገድንም በተመለከተ ጥቅም ላይ የማይውል የመንግሥት ንብረት በተገቢው ጊዜ የማስወገድ ባህል በአገራችን የተለመደ አልነበረም፡፡ በመንግሥት መ/ቤቶች ይዞታ ሥር የሚገኙ ንብረቶች ለአገልግሎት በማይፈለጉበት ጊዜ በወቅቱ ስለማይወገዱ ለዝናብና ፀሐይ ተጋልጠው በሚደርስባቸው እንግልት ዋጋቸው እየቀነሰ መንግሥት ከንብረቶቹ ሊያገኝ የሚገባውን ጥቅም የሚያጣ ከመሆኑም በላይ ለሌላ አገልግሎት ሊውል የሚገባውን ቦታ ጭምር በመያዝ ከፍተኛ ችግር አስከትሏል፡፡

4. በመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር ረገድ በተደረገው መሠረታዊ የሥራ ሂደት ለውጥ ጥናት የመንግሥት ግዥ አፈፃፀምና የንብረት ማስወገድ ሥርዓትን በከፍተኛ ደረጃ ለማሻሻል ይጠቅማሉ ተብሎ የታመነባቸው የጥናቱ ሀሣቦች የሕግ

መሠረት እንዲኖራቸው ለማድረግ ተሻሽሎ በወጣው የመንግሥት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ጸድቆ በስራ ላይ ውሏል፡፡በአዋጅ ከተካተቱት ለውጦች መካከል በመንግሥት መ/ቤቶች በወል የሚፈለጉ እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ በአንድ ማዕከላዊ ተቋም አማካኝነት አጠቃሎ መግዛት እና ንብረቶች መወገድ በሚገባቸው ትክክለኛ ጊዜ እንዲወገዱና ለመንግሥት ተገቢውን ጥቅም እንዲያስገኙ ማድረግ ናቸው፡፡

5. ከላይ የተጠቀሱትን ሥራዎች በኃላፊነት የሚመራ ራሱን የቻለ አካል ማደራጀት ተገቢ መሆኑ ስለታመነበት የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚል ስያሜ በሚኒስትሮች ምክር ቤት በወጣ ደንብ ቁጥር 184/2002 ይህ አገልገሎት እንዲቋቋም ተደርጓል፡፡

የአገልግሎቱ ራዕይ

6. በአገሪቱ ውስጥ የላቀና ተመራጭ የግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ሰጭ ተቋም መሆን፡፡

የአገልግሎቱ አላማ

7. የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዕቃዎችና አገልግሎቶች ከከፍተኛ ግዥ የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ በሚያስገኝ ተመጣጣኝ ዋጋ ፣ በተገቢው ጊዜና በተፈላጊው ጥራት እንዲቀርቡ ማስቻል፣

8. በሽያጭ እንዲወገዱ ውሣኔ የተሰጠባቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ንብረቶች በተቀላጠፈ አኳኋን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲወገዱ ማስቻልና ለመንግሥት የልማት ድርጅቶች በዕቃና አገልግሎት ግዢ እንዲሁም በንብረት ማስወገድ ረገድ እገዛ ማድረግ ነው፡፡

የአገልግሎቱ ሥልጣንና ተግባር

9. አገልግሎቱ በደንብ ቁጥር184/2002 ዓ.ም. የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል:-

- ዝርዝራቸው በሚኒስቴሩ መመሪያ የሚወሰን የመንግሥት መስሪያ ቤቶች የሚጠቀሙባቸው ተመሳሳይ ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲሁም አገራዊ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች ግዥ ያከናውናል፤
- ግምታቸው በሚኒስቴሩ መመሪያ ከሚወሰን የገንዘብ መጠን በላይ የሆነ በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ኃላፊነት ሥር ያሉ በሽያጭ እንዲወገዱ ውሳኔ የተሰጠባቸውን ንብረቶች ይሸጣል፣
- የመንግሥት ግዥና ንብረት የማስወገዱ ተግባር በአዋጁና አዋጁን ለማስፈጸም በወጡ ደንቦችና መመሪያዎች መሠረት መፈጸሙን ያረጋግጣል፣
- ለመንግሥት መሥሪያ ቤቶች እንዲሁም ጥያቄ ሲቀርብለት ለመንግስት የልማት ድርጅቶች ፣ ለክልል መንግሥታት እና ለግሉ ዘርፍ፤
- በወቅታዊ የገበያ መረጃ ላይ የተመሠረተ የአገር ውስጥና የአለም አቀፍ የግዥ አገልግሎቶች ይሰጣል፣
- የግዥ አፈፃፀምን የሚመለከት የምክርና ሥልጠና አገልገሎት ይሰጣል።

የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

የአገልግሎቱ ድርጅታዊ መዋቅር

10. የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ተጠሪነቱ ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሆኖ በስራ አመራር ቦርድ ፣ በአንድ ዋና ዳይሬክተር እና በሁለት ም/ዋና ዳይሬክተር ተዋቅሯል:: በዋናው ዳይሬክተር ሥር ስድስት የስራ ሂደቶች ማለትም የዕቅድ ዝግጅትና የአፈጻጸም ክትትል ፣ የሕግ አገልግሎት ፣ የፋይናንስ ግዥና ንብረት አስተዳደር ፣ የውስጥ ኦዲት አገልግሎት ፣ የሰው ኃብት ልማት ፣ ሪከርድና ጠቅላላ አገልግሎት እና የሕዝብ ግንኙነት አገልግሎት ያሉ ሲሆን፣ የተቀሩት አራቱ የስራ ሂደቶች ማለትም የግዥ ፣ የውል አስተዳደር ፣ የንብረት ዋጋ ግምትና ማስወገድ እና የሚወገዱ ንብረቶች መረጃና ጥናት የሥራ ሂደት በሁለቱ ም/ዋና ዳይሬክተሮች ይመራሉ።

የአገልግሎቱ የሰው ሀይል አደረጃጀት

11. ታህሳስ ስድስት ሁለት ሺህ ሰባት በተገኘው መረጃ መሰረት አገልግሎቱ 238 በመዋቅር የተፈቀደና 141 በስራ ላይ ያለ የሰው ሀይል ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ

የንብረት ዋጋ ግምትና ማስወገድ የስራ ሂደት 19 እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች መረጃና ጥናት የስራ ሂደት 15 በድምሩ 34 የተፈቀደ የሰው ሀይል ሲኖራቸው በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል ግን 9 እና 9 በቅደም ተከተላቸው መሰረት በድምሩ 18 ሲሆን ለሁለቱ የስራ ሂደት የ16 ሰው ክፍት የስራ መደብ አለው፡፡

የፋይናንስ ምንጭ

12. የመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ለሥራው ማስኬጃ የሚጠቀመው ከመንግሥት የሚመደብለትን በጀት ሲሆን በጀቱና አጠቃቀሙ እንደሚከተለው በሰንጠዥ ቀርቧል፡፡

ተ.ቁ	ገቢና ወጪ	2004ዓ.ም.	2005ዓ.ም.	2006ዓ.ም.
1.	መደበኛ በጀት	9,677,916.00	9,960,309.00	9,491,050.00
2.	መደበኛ ወጪ	7,953,607.68	8,399,769.59	(ከሐምሌ-ታህሳስ) 3,507,908.19
በጀት አጠቃቀም በመቶኛ		82.1	84.3	(ከሐምሌ-ታህሳስ) 36.96

የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ ጥናት እና የንብረት ዋጋ ግምት ማስወገድ የስራ ሂደት የአሰራር ሥርዓት መግለጫ/Process description/

13. የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ ጥናት የስራ ሂደት የሚወገዱ ንብረቶችን የተሟላ መረጃ ያጠናቅራል ፣ ለሚወገዱ ንብረቶች ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ ጥናት ያደርጋል ፣ ለመ/ቤቶች በመረጃ አያያዝ ዙሪያ ድጋፍ ይሰጣል ፣ የስራ አቅድና የአፈጻጸም ሪፖርት ያዘጋጃል፡፡ እንዲሁም የንብረት ዋጋ ግምትና ማስወገድ የስራ ሂደት ለመ/ቤቶች በንብረት አወጋገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ይሰጣል ፣ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት/ ጋር የጋራ መድረክ በማመቻቸት የመረጃ ልውውጡን ያጠናክራል ፣ የጨረታ መነሻ ዋጋ ያዘጋጃል ፣ ያለጥቅም በፌዴራል መ/ቤቶች የተከማቹ ንብረቶችን ያስወግዳል፡፡

የኦዲቱ አላማ

14. የክዋኔ ኦዲቱ አላማ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የተቋቋመበትን አላማ መሰረት በማድረግ የሚሰራው የንብረት ማስወገድ ስራ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ፣ የተዘጋጁ ሕጎች ፣ ደንቦችና መመሪያዎች መተግበራቸውን ፣ የተዘረጋው የክትትልና የቁጥጥር ሥርዓትም ተፈፃሚ መደረጉን ማረጋገጥ ሲሆን ፣ በዚህ ጉዳይ ላይ የአሠራር ግድፈቶች ካሉ መንስኤያቸውን በመለየትና የማሻሻያ ሀሣብ በመስጠት አገልግሎቱ የተሻለ አፈጻጸም እንዲኖረው እገዛ ማድረግና የመስሪያ ቤታችንን የክዋኔ ኦዲት አላማ ማሳካት ነው።

ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ

15. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አካባቢ የመንግስት መ/ቤቶች ንብረት አወጋገድን የሚመለከት ነው።

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues)

16. ከላይ ለተገለጸው የኦዲት አካባቢ ሦስት ዋና እና ስድስት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች/Audit Issues/ ተለይተዋል። እነሱም፡-

1. አገልግሎቱ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የንብረት አወጋገድን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ጠንካራ የመረጃ ማጠናከሪያና አያያዝ ሥርዓት እንዲሁም ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ አሰራርን ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፤
   1.1. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች የመረጃ አያያዝን በብቃት ለማስተዳደር እና የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደርገ መሆኑን መገምገም፤
   1.2. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ አዘገጃጀትና አፈጻጸምን መገምገም፤

2. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጨረታ ሂደትና የንብረት አወጋገድ ስርዓት አፈጻጸም ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤

   2.1. የጨረታ ሂደትን በተመለከተ፤

   2.2. የንብረት አወጋገድ ስርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ

3. አገልግሎቱ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በንብረት አወጋገድ ዙሪያ የቅኝጅታዊ አሰራር መድረኮችን በማዘጋጀት አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ እያበረከተ ስለመሆኑ መገምገም፤

   3.1. ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤

   3.2. ሙያዊ ድጋፍ አሰጣጥን በተመለከተ የሚሉት ናቸው፡፡

<u>የኦዲቱ መመዘኛ መስፈርቶች</u>

17. በኦዲት ቡድኑ የተመረጡትን ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችና ስድስት ንዑስ የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን መሰረት በማድረግ አገልግሎቱን ለመገምገም የሚያስችሉ 29(ሃያ ዘጠኝ) የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ መመዘኛ መስፈርቶቹን ለማዘጋጀት መነሻ የተደረጉት ማስረጃዎች፣ የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት የማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 184/2002 ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት የተዘጋጀ የፌዴራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ዓ.ም ፣ ከ2004 - 2006 ግማሽ ዓመት ያለ የእቅድ አፈፃፀም ሪፖርት ፣ ስትራቴጂክ እቅድ (2003-2007) ፣ የንብረት ማስወገድ ዘርፍ የውስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 3/2004ዓ.ም ፣ ከ2004 - 2006 ግማሽ ዓመት ድረስ ያለ የቦርድ እና የሥራ አመራር አባላት ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ ፣ በሚወገዱ ንብረቶች አያያዝ ዙሪያ በ40 መ/ቤቶች ላይ የተሰራ የደሰሳ ጥናት ፣ የተሰሩ የማስወገድ ስራዎች ፣ የሰው ኃይል አደረጃጀት ፣ ቃለ-መጠይቆች እና ምርጥ ተሞክሮዎች ናቸው፡፡ የተመረጡት የትኩረት አቅጣጫዎቸውና መመዘኛ መስፈርቶች ለኦዲት ተደራጊው መ/ቤት ተልከው አስተያየት ተሰጥቶባቸዋል፡፡ የተዘጋጁት የትኩረት አቅጣጫዎቸውና መመዘኛ መስፈርቶቹ ከዚህ ሪፖርት ጋር **በአባሪ 1** ተያይዘዋል፡፡

የኦዲቱ ወሰን እና ዘዴ

18. ኦዲቱ የተከናወነው የመንግሥት መ/ቤቶችን የክዋኔ ኦዲት ለማድረግ ለመሥሪያ ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 669/2002 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሆኖ ኦዲቱ የሸፈነው ጊዜ ከ2004-2006ዓ.ም. በመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት ንብረትን በማስወገድ ዙሪያ በተሰሩ ስራዎች ላይ ነው፡፡ ኦዲቱ በዋናነት የተከናወነው በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ሲሆን በመ/ቤቱ የሚገኙ ከኦዲት አካባቢው ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ መረጃዎችን በመከለስ ፣ ነሐሴ 16/2006 ዓ.ም. እና መስከረም 22/2007 ዓ.ም አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ባዘጋጀው ጨረታ ላይ ተገኝቶ በሁለቱ ቀናት ለ25 እና ለ 98 በድምሩ ለ123 ተጫራቾች መጠይቅ በመበተንና 75 ተጫራጮች ለሰጡት መልስ ትንተና በመስራት ፣ በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት ከሚያገኙ 156 የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ውስጥ ከአስተዳደርና ጠቅላላ አገልግሎት ሶስት ፣ ከኢኮኖሚያዊ አገልግሎት አራት እና ከማኅበራዊ አገልግሎት ስምንት በድምሩ አሥራ አምስት በናሙና የተመረጡ በፌዴራል ፣ በአማራ ፣ በኦሮሚያና በደቡብ የሚገኙ የመንግስት ዩኒቨርስቲዎችና የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችን ቃለ-መጠይቅ በማቅረብ ፣ ተያያዥ መረጃዎችን በመሰብሰብ ፣ በመከለስ በመተንተንና በማጠናቀር እንዲሁም የሚወገዱ ንብረቶች ባሉበት በአካል ተገኝቶ በማየት ኦዲቱ ተከናውኗል፡፡

ክፍል ሁለት

የኦዲት ግኝቶች

<u>በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት አወጋገድ መመሪያ ስለመኖሩ ፣ ለሚመለከታቸው አካላት ስለመሰራጨቱ ፣ ተግባራዊ ስለመደረጉ እና በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በመለየት ወቅታዊ ክለሳ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

19. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በንብረት አወጋገድ ዙሪያ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና እነኝህን መሰረት አድርገው የወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ ሲደረጉ በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት አፈጻጸሙን ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳብ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና በወቅቱ ተግባራዊ እንዲሆን ሊከታተል ይገባል፡፡

20. በኦዲቱ ወቅት በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የማስወገድ ስራውን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ስለመኖሩ ሲጣራ ፣ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የተዘጋጀ የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ፣ በየጊዜው የሚዘጋጁና ወቅታዊ የሚደረጉ የተለያዩ ሰርኩላሮች እና አገልግሎቱ ያዘጋጀው የውስጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 3/2004 መኖሩን፣ እንዲሁም በናሙና በታዩ ሁሉም መ/ቤቶች በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የተሰራጨ መመሪያ ቁጥር 9/2003 እና ሰርኩላሮቹ መኖራቸው ታውቋል፡፡

21. ሆኖም አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት መመሪያውን ሲያስፈጽም ለአፈጻጸም አዳግተውኛልና ቢሻሻሉልኝ ያላቸውን 12 ነጥቦች ለይቶ በደብዳቤ ቁጥር በቀን የካቲት 18/2005 በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 6/1/6/5337 እና በቀን መስከረም 30/2006 በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 6/1/03/2448 ለግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ቢያቀርብም ጥያቄው መልስ አለማግኘቱን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

22. እንዲሁም አገልግሎቱ ባዘጋጀው የሁለተኛ የአምስት ዓመት /2008 - 2012/ ስትራቴጂክ ዕቅድ ገጽ 14 እና 15 በንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003

ሊሻሻሉ የሚገባቸው የማያስሩ አንቀጾች መኖራቸውና የሚመለከተው አካል ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ አለመስጠቱ እንደችግር ተነስቷል፡፡

23. በተጨማሪም በየጊዜው የሚደርሳቸው ተለዋዋጭ ሰርኩላሮች መኖራቸውና በሰርኩላሩ መሠረት ለተለያዩ አካላት ንብረቱን ለማስረከብ የጠራ አሰራር አለመኖር ለአሰራር ችግር መፍጠሩን የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ እና የብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ የግዢና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር በጉዳዩ ላይ ለተደረገ ቃለ መጠይቅ መልስ ሰጥተዋል፡፡

24. መመሪያውን ለማሻሻል ስልጣን የተሰጠው የግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ኃላፊ መመሪያው ለምን በወቅቱ እንዳልተከለሰ በኦዲት ቡድኑ ተጠይቀው በሰጡት መልስ ፣ የፌዴራል መንግሥት የግዥና ንብረት አስተዳደደር ኤጀንሲ የግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001ን ፣ የግዥ አፈፃፀም መመሪያን እና የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 ለማሻሻል በ2006 በጀት ዓመት ጀምሮ የማሻሻያ ስራውን በማከናወን ላይ መሆኑንና በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጅቶ የነበረውን ሰነድ ከመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎትና ከሌሎች የፌዴራል መንግሥት እና የክልል ተቋማት ግብዓት ለማሰባሰብ ተዘጋጅቶ በነበረው ወርክሾኘ እንዲሁም ከየመ/ቤቶች ከተላኩ አስተያየቶች አንፃር በኤጀንሲው ደረጃ የመጨረሻ ረቂቅ ተዘጋጅቶ ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ፣ በቀጣይ ረቂቅ መመሪያው በየደረጃው ለሚመለከታቸው የመንግሥት የበላይ ኃላፊዎች ቀርቦ ሲጸድቅ ሥራ ላይ የሚውል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

25. መመሪያው በወቅቱ ባለመሻሻሉ በአሰራር ላይ የፈጠረው ክፍተት ስለመኖሩ የኦዲት ቡድኑ ለአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ መመሪያው በወቅቱ ባይከለስም በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር በየጊዜው የሚወጡት ሰርኩላሮች እያገዟቸው እንደሚገኙና መመሪያው ቢከለስ ግን ለአሰራር ምቹ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

26. ሆኖም ኤጀንሲው የአገልግሎት ሰጪውንና ከተለያዩ መ/ቤቶች ያሰባሰባቸውን የማሻሻያ ሀሳቦች አዋጪነታቸውን በማጥናት በወቅቱ በመከለስ ፋንታ በየጊዜው ሰርኩላርን እያዘጋጁ መበተኑን እንደአማራጭ መጠቀሙ ፣ ሰርኩላሮቹ ሁሉንም

እንዲሻሻሉ የተፈለጉትን ሀሳቦች የማያጠቃልሉ ከመሆናቸውም በላይ በየጊዜው ሰርኩላር እያዘጋጁ ለሁሉም የፌዴራል መ/ቤቶችና የመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መበተኑ ስራውን ከጊዜና ከወጪ አንጻር አዋጭ እንዳይሆን ፣ ተደራሽነቱ ጥያቄ ውስጥ እንዲወድቅ እና ወጥ አሰራር እንዳይኖር እንዲሁም ከግንዛቤ እጥረት የተነሳ ለስራ አፈጻጸም ክፍተት የሚፈጥር በመሆኑ ኤጀንሲው መመሪያውን በወቅቱ አለመከለሱ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>አገልግሎቱ የሚያስወግዳቸውን ንብረቶች ዝርዝር በመረጃ ቋት /data base/ በመያዝ የሚወገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ በስትራቴጂክና በአመታዊ እቅድ ማስቀመጡንና አፈጻጸሙን መከታተሉን በተመለከተ፤</u>

27. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት በሚሰጣቸው መ/ቤቶች እና የትምህርት ተቋማት መወገድ የሚገባቸውን ንብረቶች መረጃ በመረጃ ቋት /data base/ በመያዝ የሚወገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ በስትራቴጂክ እቅድ አካቶ በየበጀት አመቱ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለማከናወኑ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያዘጋጅ እና ክንውኑ ከእቅዱ ካነሰ ምክንያቱን በመለየት በአፈጻጸም ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡

28. ይሁን እንጂ በኦዲቱ ወቅት በተደረገ የማስረጃ ክለሳና ለመ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች በቀረበ ቃለ መጠይቅ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በየዓመቱ የምን ያህል መ/ቤቶችን ፣ ስንት ተሽከርካሪና ንብረት እንደሚያስወግድ በስትራቴጂክ እቅዱ (2002-2007) ዓ·ም እንዳላስቀመጠ ለማወቅ ተችሏል፡፡

29. በተጨማሪም በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና በመንግስት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙትንና መወገድ ያለባቸውን ተሽከርካሪዎችና ንብረቶች በቅደም ተከተል ለማስወገድ የሚያስችል የመረጃ አሰባሰብ ስርዓት በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት እንዳልተዘረጋ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

30. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ እቅዱን ለማቀድ ስራው ግብዓትን መሰረት ያደረገ በመሆኑ ቀድሞ የዚህን መ/ቤት ይህን ያህል አስወግዳለሁ ማለት አስቸጋሪ መሆኑንና በቅደም ተከተል ለማስወገድም የማይቻለው ንብረቱ ለአደጋ ተጋላጭ ይሆናል ተብሎ ሲታሰብና

ከፍተኛ የንብረት ክምችት ያለባቸውን መ/ቤቶች ለማስወገድ ቅድሚያ የሚሰጥበት አሰራር በመኖሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

31. ሆኖም ስራው ግብዓትን መሰረት ያደረገ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ አስቀድሞ አለማቀድ አፈጻጸምን ለመለካት የማያስችል በመሆኑና ግብዓቶችን አስቀድሞ በመሰብሰብ ለአወጋገድ በቅደም ተከተል አለማስቀመጥም ስራውን ወጥ እንዳይሆንና ሁሉም ተገልጋይ አገልግሎቱን በእኩል እንዳያገኝ የሚያደርገው በመሆኑ አሰራሩ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>አገልግሎቱ ንብረት በሚያስወግድላቸው መ/ቤቶች የሚወገድ ንብረት መኖሩን ለማረጋገጥ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ ስለመላኩና መልስ ስለመስጠታቸው ክትትል ማድረጉን በተመለከተ፤</u>

32. በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት እንዲያገኙ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ዝርዝራቸው የቀረበ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገድ ንብረት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በአመት ሁለት ጊዜ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ የመላክና መልስ መስጠታቸውን ክትትል የማድረግ ስራ በአገልግሎቱ ሊሰራ ይገባል፡፡

33. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገድ ንብረትና ተሽከርካሪ መረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ በአመት ሁለት ጊዜ እንደሚልክና ቅጹ የተላከላቸውም መ/ቤቶች ወቅታዊ ምላሽ እንዲሠጡ በስልክ ክትትል እንደሚያደርግ በስትራቴጂክ እቅዱ (2002-2007) አስቀምጧል፡፡

34. በዚሁ መሰረት ኦዲቱ በሚሸፍነው ጊዜ ውሥጥ (2004-2006 በ.ዓ.) ለመ/ቤቶች የተላከውን ቅጽ በተመለከተ እቅዱ ከአፈጻጸሙ ጋር ስለመጣጣሙ በተደረገው የሰነድ ክለሳ፣ በሐምሌ 22/05 ለ 34 ፣ በሐምሌ 23/05 ለ 42 ፣ በህዳር 06/06 ለ 21 ፣ በህዳር 06/06 ለ19 ፣ በታህሣሥ 30/06 ለ17 እና በታህሣሥ 30/06 ለ18 ፣ መ/ቤቶች በደብዳቤ ቁጥር ግንማ13/2/18/429 ፣ ግንማ 13/2/7/428 ፣ ግንማ13/2/247/3453 ፣ ግንማ13/2/247/3454 ፣ ግንማ13/2/30/667 ፣ ግንማ 13/2/302/6673 ፣ እና ግንማ13/2/070/355 እንደ ቅደም ተከተላቸው የተላከ ሲሆን ይህም በ2004 እና በ2005 በጀት ዓመት ለየትኛውም መ/ቤት ቅጹ

አለመላኩን በ2006 በጀት ዓመት ያለውም አፈጻጸም ሲታይ አገልግሎት ከሚያገኙ 156 መ/ቤቶች ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ቅጹ እንዳልደረሳቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

35. በተጨማሪም ከፍተኛ ያልተወገዱ ንብረት ክምችት አለባቸው ተብሎ የተገለጹ መ/ቤቶች የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ እንዲልኩ ደብዳቤ ተልኮላቸው አንድ መ/ቤት ብቻ መረጃ መላኩን በስራ አመራር ቃለ ጉባኤ የዶክመንት መለያ ቁጥር 63 ላይ ተገልጿል፡፡

36. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ ቅጾቹ በተያዘላቸው ጊዜ እንደሚላኩና ክትትሉም በስልክ እንደሚደረግ ገልጸዋል፡፡

37. ሆኖም በመ/ቤቶች የተከማቸና የሚወገድ ንብረት እያለ ማስረጃ ማሰባሰቢያው ቅጽ ወቅቱን ጠብቆ አለመላኩ ፣ ለተላከላቸውም መ/ቤቶች መረጃውን እንዲልኩ የሚደረገው ክትትል ስልክ ብቻ መሆኑ፣ አወጋገዱ ላይ መዘግየትን የሚፈጥር በመሆኑ አሰራሩ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚገኙና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ መወገዳቸውን በተመለከተ፤</u>

38. በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከማችተው የሚገኙና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ ሊወገዱ ይገባል፡፡

39. በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በቀረቡለት ማስረጃዎች መሰረት በማስወገድ ስራው ላይ ክፍተት የፈጠሩበት የሚከተሉት ምክንያቶች ታይተዋል፡፡

- በመመሪያ ቁ.9/2003 የማስወገጃ ጊዜ ገደብ አለመኖርና የሚወገዱ ንብረቶች በከፍተኛ ክምችት በአብዛኛው መ/ቤቶች መገኘት፣
- በተለያዩ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች ለዘመናት ተከማችተው የሚገኙ ንብረቶች እንዲወገዱ በወቅቱ ውሳኔ አለመስጠትና ለአገልግሎቱ ትክክለኛ መረጃ አለመላክ፣
- የጨረታ መነሻ ዋጋ ለማዘጋጀት እና ኮድ ለመለጠፍ ወደ 4 መስሪያ ቤቶች በተሄደበት ወቅት በሚወገዱ ንማዎች የአቀማመጥ ችግር እንደነበራቸው፤

ለምሳሌ የትራንስፖርት ባለሥልጣን ፣ የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ ፣ የብረታብረት እንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት እና የመንግሥት ማህበራዊ ጉዳይ ኤጀንሲ ሲሆኑ በተለይ በትራንስፖርት ባለሥልጣን 1 መደብ ሳይኖር መተማመኛ የመፈራረም እና ካሊመዳሪዎችን ሳይለዩ ከሚወገዱት ጋር አብረው መገኘታቸውን እንዲሁም በብረታ ብረት እንዱስትሪ ልማት ኢንዱስትሪ የሚወገዱት እና የማይወገዱትን ንብረቶችን ተቀላቅለው መገኘታቸው፣ ንብረት እንዲወገድላቸው ከሚጠይቁ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች የሚላከው መረጃ የተሟላ አለመሆን፣ በፌዴራል መስሪያ ቤቶች ለሚወገዱ ንብረቶች አያያዝ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ ከመሆኑ የተነሳ በመረጃ አሰባሰብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩ፣

- የተለያዩ ንብረት የሚወገድላቸው መስሪያ ቤቶች በአግባቡ ትብብር አለማድረጋቸው፣ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከገንዘብና ኢኮኖሚ ሚኒስቴር ኮምፒውተር እና ኤሌክትሮኒክስ ዕቃዎችን እንዲያነሱ በተሰጣቸው ውክልና መሠረት በወቅቱ አለማንሳት እና ለአገልግሎቱ ሪፖርት አለማቅረብ፣
- አንዳንድ መ/ቤቶች ለዋጋ ግምትና ኮድ ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ትብብር አለማድረግ ለምሳሌ የማዕከለዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲና የፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በሽያጭ እንዲወገዱ የቀረቡትን ተሽከርካሪዎች ለተጫራቾች እይታ በሚያመች መልኩ ለማደራጀት ፈቃደኛ አለመሆን፣
- የተለያዩ ንብረቶች ለማደራጀት ወደ መ/ቤቶች በአካል ሲኬድ አስፈላጊ ትብብር አለማድረግ ለምሳሌ፣ ብቃት ያላቸው ቴክኒሻኖች አለመመደብ፣
- የባለንብረት መ/ቤቱ የሚወገዱ ልዩ ልዩ ንብረቶችን በአንድ ጊዜ አሰባስቦ ከመላክ ይልቅ እየከፋፈሉ በተለያየ ጊዜ መላክ፣
- የጨረታ መነሻ ዋጋ ለማዘጋጀት እና ኮድ ለመለጠፍ ወደ 4 መስሪያ ቤቶች በተሄደበት ወቅት በሚወገዱ ጎማዎች የአቀማመጥ ችግር የነበራቸው መሆኑ፣
- በመስሪያ ቤቶች እንዲወገዱ ውሣኔ የተሰጠባቸው ንብረቶች አስፈላጊ መረጃዎች ባለመሟላት ምክንያት በማስወገዱ ሂደት ላይ በሚፈለገው ፍጥነትና ቅልጥፍና ላይከወን ይችላል የሚል ስጋት በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት መኖር፣

- በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በቀረበው ማስረጃ መሰረት ከ2004 - 2006 በጀት አመት ባለው ጊዜ ውስጥ አገልግሎቱ ያስወገዳቸው ንብረቶችና ተሽከርካሪዎች በንጽጽር ሲታዩ ተሽከርካሪ የተወገደላቸው መ/ቤቶች ብዛት 120 ሲሆን ንብረት የተወገደላቸው ደግሞ 33 መሆኑ፣

40. እንዲሁም ጸረ-ሙስና ኮሚሽን በመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች የንብረት አስተዳደር ለሙስናና ብልሹ አሰራር ያለው ተጋላጭነት ላይ ለውይይት መድረክ መነሻነት ባዘጋጀው የዳሰሳ ጥናት ሪፖርት፤

- ስራውን ለመስራት የሚያስፈልጉ ሙያተኞች በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ የሌላቸው መሆኑን፣
- ማንም ሊሰራው ይችላል በሚል አመለካከት ለስራው ተገቢው ባለሙያ የማይመደብበት ፣ ስራውም በተለምዷዊ ሁኔታ የሚሰራና ትልቅ ተቋማዊ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑን፣
- በአብዛኛዎች የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎች በንብረት አስተዳደር ስለሚሰሩ ስራዎች ተገቢውን ትኩረት እንደማይሠጡና መረጃዎች የሌላቸው መሆኑን፣
- ለቦታው ሰራተኞች ምንም የትምህርት ዝግጅትና የስራ ልምድ የማይጠየቅበት ሁኔታ መኖሩን እንዳንዴም በቅጣት የሚመደቡበት መሆኑን በጥናቱ አስቀምጧል።

41. እንዲሁም የግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በ30 መስሪያ ቤቶች ላይ ባደረገው የግዢና ንብረት ኦዲት 19ኙ መ/ቤቶች በወቅቱ መወገድ የሚገባቸውን ንብረቶች አለማስወገዳቸውን፣ በ2006 የ9 ወር ሪፖርቱ ላይ አስፍሯል።

42. በተጨማሪም በኦዲቱ በናሙና ተመርጠው ከታዩና ቅጹ ከተላከላቸው መ/ቤቶች ውስጥ የሚወገድ ንብረት እያላቸው በተላከላቸው ቅጽ መሰረት የሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች የንብረቶቹን ዝርዝር በወቅቱ ለአገልግሎቱ ለምን እንዳላሳወቁ የኦዲት ቡድኑ ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ ከሰጡት መልስና፣ ቦታው ላይ በመገኘት ካየው የሚወገዱ ንብረቶች ተነስቶ የሚከተሉትን ማስረጃዎች አሰባስቧል፤

ሀዋሳ ዩኒቨርስቲ፣

- በደረሰው ቅጽ መሰረት በደብዳቤ ቁጥር ሀዩ/04/7452/06 በቀን 14/12/2006 47 የተለያዩ አሮጌ የተሽከርካሪ ባትሪዎች ፣ 290 ጎማዎችና 7000 ኪ.ግ. የሚመዝን የተሰባበረ ውድቅዳቂ ብረታ ብረቶችን እንዲወገዱለት ለአገልግሎቱ ማሳወቁን፣
- የኦዲት ቡድኑ ቦታው ላይ በመገኘት 9 ተሽከርካሪዎች ፣ 2 ሞተር ሳይክል ፣ 4 ትራክተር ፣ በሁለት ሳጥን የተቀመጡ የተሸጡ መኪኖች መለዋወጫዎች በማየቱ ለምን እንዳልተወገዱ ባነሳው ጥያቄ ዩኒቨርስቲው በማዕከል የሚያስተዳድር በመሆኑ ከየካምፓሶቹ ተጨማሪ ንብረቶችን በማሰባሰብ ላይ መሆኑንና አሰባስቦ ሲጨርስ ለአገልግሎቱ እንደሚያሳውቅ፣

በሀዋሳ ዩኒቨርስቲ በዩኒቨርስቲው ግቢ በሜዳ ያሉ የሚወገዱ ንብረቶች

ቅዱስ ጴጥሮስ /የሳንባ ነቀርሳ/ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል፣

- ከአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ባለሙያዎችን አምጥተው ንብረቶቹን እንዳሳዩና ለቁርጥራጭ ብረቶች ሰርኩላር እስኪደርሳችሁ ጠብቁ በተባሉት መሠረት ሰርኩላሩ መጋቢት 15/2006 ደርሷቸው ለሥራው ኮሚቴ አዋቅረው በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፤
- መሣለሚያ ኮልፌ የሚገኘው ቅዱስ ጴጥሮስ የተመላላሽ ሕክምና መስጫ በተዘጋበት ወቅት የሆስፒታሉ ንብረት ወደዚህኛው ሆስፒታል ሲመጣ ንብረቶቹ አገልግሎታቸውን የጨረሱና ረጅም አመት ያስቆጠሩ በመሆናቸው ንብረቶቹን በመለየት አገልግሎት ይሰጣሉ የሚባሉትን ወደመጋዘን ለማስገባትና አገልግሎት የማይሰጡትን ለማስወገድ ሥራዎችን እየሰሩ መሆናቸውን፣

በቅዱስ ጴጥሮስ ሆስፒታል አንድ ክፍል ይዞ የተቀመጠ የሚወገድ ንብረት

ጥቁር አንበሳ ሪፈራል ሆስፒታል፣

- በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የሚላከው የሚወገድ ንብረት ማሰባሰቢያ ቅጽ ለሁለተኛ ጊዜ እንደደረሳቸውና የመጀመሪያው በተላከበት ወቅት የህንጻ እድሳት ላይ ስለነበሩ የንብረቶቹን መረጃ ለማሰባሰብ ጊዜ እንዳላገኙ ፣ በድጋሜ ለተላከው ግን ስራውን ለማሳካት እንቅስቃሴ ላይ መሆናቸውን፣
- በሆስፒታሉ በርካታና ምንነታቸውን ለማወቅ የሚያስቸግር በሁለት መጋዘን የተከማቹ ንብረቶች ቢኖሩም ንብረቱን ለማስወገድ የንብረት ክፍል ኃላፊዋ ቦታው ላይ ከመጡ ገና አንድ አመት መሆኑንና ስራው እስከዛሬ እንዳልተሰራ ሆኖም በጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁትን አወዳድረው በመቅጠር ንብረቶቹን የመለየት ስራ ለመስራት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣

የኢትዮጵያ ኢነርጂ ባለስልጣን፣

- ዋጋቸው ከመቶ ሺ ብር በታች የሆኑ ንብረቶች በቀን 8/9/2006 በባለሥልጣን መ/ቤቱ መወገዱና አሮጌ እቃዎችን ማደራጀትና ዋጋ ማውጣት ግን ለኮሚቴው አድካሚ ስራ እንደነበር፣ ሆኖም አሁን የተከማቸ ንብረት አለመኖሩንና የሚወገድ ንብረት እንደሌላቸው ለአገልግሎቱ በደብዳቤ ማሳወቃቸውን፣
- በቁጥር 13 የሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች መኖራቸውንና የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር እንዲያስወግዳቸው በደብዳቤ የተጠየቀ መሆኑን፣

ደብረብርሀን ዩኒቨርስቲ፣

- ከዚህ በፊት በአገልግሎቱ ንብረት እንደተወገደላቸው ሆኖም ሁለት ጊዜ ተጫርተው ገዢ ያላገኙ ንብረቶች መኖራቸውን፣
- የሚወገዱትንና እንደገና ተጠግነው አገልግሎት ላይ የሚውሉትን ንብረቶች ለመለየት ጊዜ እንደወሰደባቸው ሆኖም አሁን ቁጥራቸው 1204 የሆኑ የቢሮ መገልገያ እቃዎችንና 275 የተለያዩ ንብረቶችን ዝርዝር ለአገልግሎቱ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን፣

በደብረብርሀን ዩኒቨርስቲ በመጋዘን የተቀመጡ የሚወገዱ ንብረቶች

- ቁጥራቸው 508 የሆኑ አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ለመላክ ዝርዝር መረጃ ያዘጋጀ መሆኑን፣

በደብረብርሀን ዩኒቨርስቲ እንዲወገዱ የተዘጋጁ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች

- በቁጥር 210 የሆኑ የተለያዩ ያገለገሉ የመኪና ጎማና ባትሪዎች እንዲወገዱ ዝርዝር መረጃቸውን በደብዳቤ ቁጥር ደዩደማ/1933/4-21/36 በቀን 21/12/2006 ዓ.ም. ለአገልግሎቱ መላካቸውን፣
- እንዲሁም ከትምህርት ሚኒስቴር የተላኩና በቁጥር 90 የሆኑ የተለያየ መጠን ያላቸው የኤሌክትሪክና የጋዝ ምድጃዎች ፣ የኤሌክትሪክ ወጥ መስሪያዎች(ድስቶች) እና ልዩ ልዩ የወጥ ቤት ቁሳቁሶች በተሻለ መገልገያ እቃ በመተካታቸው ንብረቶቹ ያለአገልግሎት ሰፊ ክፍል ይዘው መቀመጣቸውንና እነዚህን ንብረቶች ለማስወገድ የገቢ ደረሰኝ ያልተቆረጠላቸው /ሞዴል 19/ በመሆኑ በአሰራር ላይ ክፍተት መፍጠሩን፣
- ይህንኑ ጉዳይ ለማጣራት የኦዲት ቡድኑ በትምህርት ሚ/ር ለሚገኙ ጉዳዩ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ንብረቶቹ 13ቱ ዩኒቨርስቲዎች በተሰሩ ወቅት ለ13ቱም የተገዙና የተሰራጩ መሆናቸውን ፣ ደብረብርሀን ዩኒቨርስቲም ንብረቶቹን በትክክለኛው መንገድ ለመረከቡ መረጃ እንዳላቸው ገልጸዋል፡፡
- ሆኖም የኦዲት ቡድኑ የቀረበለትን መረጃ ሲከልስ ያገኘው፣ ብሪጅቴክ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ንብረቱን ለዩኒቨርስቲው ማምጣቱንና ዩኒቨርስቲውም

እቃውን በቀን 1/7/2000ዓ.ም በአደራ መረከቡን የሚገልጽ ደብዳቤ ለብሪጅቴክ ኃ.የተ.የግ.ማህበር ማቅረቡን ነው፡፡

በደብረ-ብርሀን ዩኒቨርስቲ ያለአገልግሎት በመጋዘን የተቀመጡ የወጥ ቤት ቁሳቁሶች

ፍትህ ሚኒስቴር፣

- ቁጥራቸው 186 የሆነ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እንዲወገዱላቸው በቀን ህዳር12/05 ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ቢልኩም ምላሽ አለማግኘታቸውን የሚገልጽ ማሥረጃ መቅረቡ፣
- በቀን ጥር6/06 በተጻፈ ደብዳቤ 3ተሸከርካሪዎችና 3 ሞተር ሳይክሎችን እንዲወገዱለት ለአገልግሎቱ ማሳወቁ፣
- የኦዲት ቡድኑ በሁለት ኮንቴነር ተከማችተው ስላያቸው ንብረቶች ምንነት ላነሳው ጥያቄም ሚኒስቴር መ/ቤቱ የቅርንጫፍ መ/ቤቶችን በማእከል የሚያስተዳድር በመሆኑ ከቅርንጫፍ መ/ቤቶች ያሉትን ሁሉ በማሰባሰብ ማስረጃውን አጠናቅረው ለአገልግሎቱ እንደሚያሳውቁ፣

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣

- ብዛታቸው 1200 የሆነ አገልግሎት የማይሰጡ ኮምፒውተሮች እንዲወገዱ መረጃቸው ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መላኩን፣
- የ38 ተሽከርካሪዎችን መረጃ ለመንግሥት ግዥና ንብረት ማስወገድ አገልግሎት በመላክ 23 ተሽከርካሪዎች እንዲወገዱ መደረጉና ፣ ቀሪዎቹ 15 ግን እስካሁን ድረስ ያልተወገዱ ቢሆንም በዚህ አመት ተጨማሪ ከሚወገዱ ተሽከርካሪዎች ጋር ዝርዝርራቸውን በመላክ እንዲወገዱ እንደሚደረግ፣

የውሃ ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚኒስቴር፣

- በቁጥር 8492 የሆኑ ያገለገሉ ልዩ ልዩ እቃዎች በቀን መስከረም/20/06 እንዲሁም በቁጥር 35 የሆኑ ተሽከርካሪዎች በቀን ጥቅምት 20/2005 የተወገዱ መሆናቸውን የሚያሳይ ማስረጃ ማቅረባቸው፣ ተሽከርካሪዎቹን ለማስረከብ ግን የአንዳንዶቹን መረጃ ለማሟላት እስከ ስምንት ወር ጊዜ የፈጀ መሆኑን፣
- ያልተወገዱ ሌሎች ንብረቶች በመኖራቸው መረጃውን ለአገልግሎቱ ማቅረባቸውንና ለማስወገድ ተራ እየጠበቁ መሆናቸውን፣ ሆኖም የንብረት ክፍል ሰራተኛው ለቅቆ አሁን በስፍራው ሰው አለመኖሩን፣

የኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ኤጀንሲ፣

- ከዚህ በፊት በቀን 16/07/05 7 ተሽከርካሪዎችና በቀን 09/07/06 540 የመኪና ባትሪና ጎማዎች የተወገዱላቸው በመሆኑ፣ ለተላከው ደብዳቤው መልስ ለመስጠት ለጊዜው የተከማቸ ንብረት እንደሌለና አገልግሎት የማይሰጡትን ከየስራ ክፍሉ እያሰባሰቡ መሆናቸውን፣
- ሆኖም የኦዲት ቡድኑ በምልከታ ባገኘው መረጃ ከአገልግሎት ውጪ የሆኑ አምስት የህትመት መሳሪያዎችንና ሌሎች ንብረቶችን በመጋዘን ተቀምጠው በማየቱ ባነሳው ጥያቄ የብረታብረትና ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽን ንብረቶቹን ሊያነሳቸው ሲመጣ ግዙፍ ከመሆናቸው የተነሳ ሊያነሳቸው አለመቻሉንና በኋላም ለአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት እንዲወገድ አለማሳወቃቸውን፣ ለቦታው አዲስ መሆናቸውም ክፍተቱን እንደፈጠረ፣

የፌዴራል ማረሚያ ቤቶች አስተዳደር፣

- የባለቤትነት ሊብሬ የሌላቸው 8 ተሽከርካሪዎች ሊብሬያቸው ካለ እንዲሰጣቸው ለ10ሩ ክፍለ ከተማ የመንገድ ትራንስፖርት ጽ/ቤት በቀን 05/06/06 የተጻፈ ደብዳቤ በማስረጃ መቅረቡ፣
- ከ23 ዓመት በላይ እድሜ ያላቸውና አገልግሎት ያቆሙ ሁለት የዳቦ ማሽኖች፣ እንዲወገዱለት በቀን 20/05/06 አገልግሎቱን የጠየቀበት ማስረጃ መቅረቡ፣

ብሔራዊ ሜትሮሎጂ ኤጀንሲ፣

- ሊወገዱ የሚገባቸው ነገር ግን ያልተወገዱና ከ20 አመት በላይ እድሜ ያስቆጠሩ ልዩ ልዩ ንብረቶች ፣ ጐማና ባትሪ ፣ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች ፣ ብረታብረት ፣ የኮሚኒኬሽን ሬዱዩኖች ፣ ማቀዝቀዣ የመሳሰሉት ባሏቸው 11 ቅርንጫፍ መ/ቤቶች መኖራቸውን፣



በብሔራዊ ሜቲዎሮሎጂ ኤጀንሲ ግቢ ውስጥ የተከማቹ ንብረቶች በሜዳ ላይ በከፊል

ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ፣

- ቁጥራቸው 215 የሆነ ኮምፒውተሮችና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎች እንዲወገዱላቸው በቀን 06/05/06 ለመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር መረጃ ቢልኩም መልስ አለማግኘታቸውን የሚገልጽ ማሥረጃ መቅረቡ፣
- በስቶር የተከማቹ አገልግሎት የማይሰጡ የህክምና መገልገያ እቃዎች (ሴክሽን ማሽን ፣ አንስቴዢያ ማሽን ፣ ኢንኩቤተር ፣ አልትራሳውንድ ፣ ዋርመር ፣ የህጻናት ኦክስጂን እና የተለያዩ የላቦራቶሪ እቃዎች) መኖራቸውና ለማስወገድ የባለሙያ እገዛ እየጠበቁ መሆናቸውን፣

አዳማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርስቲ፣

- ስላሉት ንብረቶች በተደረገው ቃለ-መጠይቅ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በሐምሌ 14/06 በደብዳቤ ቁጥር ግንማ 13/2/070/355 በላከው ቅጽ መሰረት 3 ተሸከርካሪ ፣ 263 ጎማዎች ፣ 88 ባትሪዎች 4 ሞተር ሳይክሎችን በቅጹ አስፍሮ ለአገልግሎቱ መለኩ በመረጃ ታይቷል፡፡

- ዩኒቨርስቲው ወርክሾፕ ያለው በመሆኑ የተሰባበሩ እንጨቶችንና ብረታብረቶችን እንዲሁም ሌሎች ቁሳቁሶችን ከማስወገድ ይልቅ በግብዓትነት

የሚጠቀምበት በመሆኑ ከላይ ከተገለጹት ውጪ የሚወገዱ ንብረቶች እንደሌሉት፣

የአዳማ ዩኒቨርስቲ ዩኒቨርስቲ ወርክሾፕ

የመንግሥት ቤቶች ኤጀንሲ፣

- በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ቁጥራቸው 832 የሆነ ንብረት እንደተወገዱለትና ካለው የንብረት ብዛት ጋር ሲነጻጸር የተወገደው አንድ መቶኛ ያህል መሆኑን፣
- በ6 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ከሚታደሱ ቤቶች ተመላሽ የሆኑ የተከማቹ ንብረቶች ተዘርዝረው መኖራቸውንና በጥያቄአቸው መሰረት ከመኪኖቹ ውጭ ያሉትን ንብረቶች ራሳቸው እንዲያስወግዱ በደብዳቤ ቁጥር ግንማ1332/671/13466 በቀን ሰኔ 3/2006 ዓ.ም. በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ውክልና ማግኘታቸውን፣
- ንብረት የማሰባሰብ ሥራው አድካሚና ሥጋት ያለው በመሆኑ ኮሚቴዎችን በስራው ለማሳተፍ ምንም አይነት ማበረታች ስለሌለው አሮጌ እቃዎችን ማስተካከል ጊዜ መውሰዱን፣

ከ6ቱ ቦታዎች በአንዱ በሜዳ ላይ የተቀመጠ የመንግስት ቤቶች ኤጀንሲ የሚወገድ ንብረት

43. በተጨማሪም ከየመስሪያ ቤቶች ኮምፒውተሮችንና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን እንዲወስድ ስልጣን የተሰጠው የመገናኛኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ንብረቶቹን ለምን እንደማያነሳ የአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ኃላፊዎች የኦዲት ቡድኑ በተገኘበት ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ላቀረበው የቃል ጥያቄ እስከአሁን የሰበሰባቸው ብዙ እንደሆኑና ተጨማሪ ለመሰብሰብ ያለው ቦታ ውስን በመሆኑ እንደማያስችለው ሆኖም ለዚሁ ስራ በመገንባት ላይ ያለው ህንጻ ሲጠናቀቅ ማሰባሰብ እንደሚጀምር ገልጸዋል፡፡

44. የኦዲት ቡድኑ ባሰባሰበው መረጃ መሰረት በየመ/ቤቶቹ የሚገኙ የስራ ኃላፊዎች ስለሚወገዱት ንብረቶች ተፈላጊውን መረጃ በወቅቱ በማሰባሰብ አፋጣኝ እርምጃ አለመውሰዳቸውን ነው፡፡ ይህ ደግሞ ንብረቶቹን ለከፋ ብልሽት፣ ለአካባቢ ብክለት ፣ ለስርቆት እንዲጋለጡና ለሌላ አገልግሎት ሊውል የሚገባውን ቦታ ከመያዙም በላይ ለክፍሉ ሰራተኞች በየአመቱ በሚደረገው ቆጠራ የስራ ጫና የሚፈጥር በመሆኑና በሽያጭ የሚወገዱትም በወቅቱ ቢሸጡ የሚያስገኙት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከፍተኛ በመሆኑ በተለያየ ምክንያት ስራው መዘግየቱ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ አገልግሎቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የሰው ኃይል ያለው መሆኑን በተመለከተ፤

45. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ አገልግሎቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲችል የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ያገኘና በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡

46. በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ወቅታዊ ተደርጎ በቀረበው መረጃ መሰረት ሁለቱ የስራ ሂደት (የንብረት ዋጋ ግምትና ማስወገድ እና የሚወገዱ ንብረቶች መረጃና ጥናት) ለ34 ሰው የስራ መደብ ሲኖረው አሁን በስራ ላይ ያለው የሰው ኃይል 18 ብቻ መሆኑ በኦዲቱ ታውቋል፡፡

47. ስለጉዳዩ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት መልስ መ/ቤቱ እንደተቋቋመ ያለው የሰው ኃይል ለስራው በቂ እንደነበር አሁን ግን ስራው እየሰፋ በመሄዱ እንደስራ ሂደት ብቻ ሳይሆን እንደ መ/ቤትም የሰው ኃይል መቅጠር ያስፈልግ እንደነበርና የሚቀጠረውን የሰው ኃይል ለስራ ለማሰማራት ግን የቢሮ ችግር መኖሩን፣ ይህንኑ ችግር ለማቃለልም ተጨማሪ ቢሮዎችን ለመስራት የማስፋፊያ ስራው በጅምር እንዳለና ቢሮዎቹ ሲገነቡ ችግሩ እንደሚፈታ አብራርተዋል፡፡

48. ይሁንና የኦዲት ቡድኑ በናሙና መርጦ በቦታው በመገኘት ባያቸው የመንግስት መ/ቤቶችና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተከማቹና ለከፋ ብልሽት እየተጋለጡ ያሉ ፣ ለመ/ቤቶቹም ቦታዎችን በመያዝ ለአያያዝና አጠባበቅ ችግር የፈጠሩና በአፋጣኝ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች በመኖራቸውና ፣ ሲወገዱም የሚያመጡት ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ የጎላ በመሆኑ ስራውን ማፋጠን የሚችል የተሟላ የሰው ኃይል በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አለመገኘቱ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ለሚወገዱ ንብረቶች የተሰራ ቀመር መኖሩን በተመለከተ፤

49. በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለሚወገዱ ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ እንዲኖር ቀመር ሊዘጋጅላቸው የሚችሉ የንብረት አይነቶችን በጥናት በመለየት ቀመር ሊዘጋጅላቸው፣ ቀመር ሊዘጋጅላቸው የማይችሉ ንብረቶችንም ወጥ በሆነ አሰራር እንዲወገዱ ለማድረግ በግልጽ የተቀመጠ የአሰራር መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡

50. በኦዲቱ በተከለሰው ማስረጃ መሰረት ለተሽከርካሪ የተቀመጠ ቀመር በመኖሩ ለሚወጣው ጨረታ የመነሻ ዋጋ ተዘጋጅቶለት ተጫራቹ ያንን መሰረት በማድረግ የሚጫረት መሆኑን ፤ ከተሽከርካሪ ውጪ ላሉ ንብረቶች ግን ቀመር አለመኖሩንና አገልግሎቱ ወቅታዊ የገበያ ጥናት አድርጎ ያዘጋጀውን ዋጋ በማየት ተጫራቹን እንደሚያወዳድር ታውቋል፡፡

51. በተጨማሪም የኦዲት ቡድኑ ከከለሰው ማስረጃ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ስለጉዳዩ የሚከተትን እንደችግር አስቀምጧል፡፡

- ለሚወገዱ ልዩ ልዩ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ መነሻ ዋጋ ለማዘጋጀት ቀመር አለመኖር፣ /ስትራቴጂክ ዕቅድ /2008- 2012/ ገጽ 14 እና 15/
- አንዳንድ አምራቾችም ሆነ አስመጪ ድርጅቶች ወቅታዊ የገበያ ዋጋ ሲጠየቁ ለመስጠት ፍቃደኛ አለመሆን፣ ቢሰጡም ደግሞ የተጋነነ ዋጋ ወይም የወረደ ዋጋ መስጠታቸውን፣ /የ2005 የመጀመሪያ ሩብ አመት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት/
- ለእያንዳንዱ የሚወገዱ ንብረቶች የወቅቱን የመተኪያ የገበያ ዋጋ አለማግኘት ከዚህም የተነሳ የጨረታ መነሻ ዋጋ ማዘጋጀት አለመቻል፣ /ስትራቴጂክ ዕቅድ 2008- 2012 ገጽ 14 እና 15/

52. እንዲሁም የመ/ቤቱ ኃላፊዎች ንብረቶችን ለማስወገድ ቀመር ለምን እንዳልተሰራ የኦዲት ቡድኑ ላቀረበው ቃለመጠይቅ በሰጡት መልስ፣ ለአሁኑ ቀመሩ አለመኖሩን ቢሰራ ግን ለአሰራር የሚያመች በመሆኑ ሀሳቡን እንደግብዓት እንደሚጠቀሙበት ገልጸዋል፡፡

53. ሆኖም አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በየጊዜው ለሚያስወግዳቸው ንብረቶች ዋጋቸውን በቀመር ከመስራት ይልቅ የመተኪያ ዋጋ ለማግኘት የገበያ ጥናት ማድረጉ የማስወገዱ ስራ ረጅም ጊዜ እንዲወሰድ ፣ ወጪው እንዲጨምር እና ወጥ አሰራር እንዳይኖር አድርጎታል ፡፡

አገልግሎቱ ለሚወገዱ ንብረቶች የሚያወጣቸው ጨረታዎች ተሳታፊዎችን ሊደርስ የሚችል መሆኑን በተመለከተ፤

54. አገልግሎቱ ለሚወገዱ ንብረቶች የሚወጡ ጨረታዎችን ጥሪ የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ተሳታፊዎችን ለመድረስ የሚችል ሰፊ ሽፋን ያለው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የመ/ቤቶችን ንብረትና ተሽከርካሪ ለማስወድ የሚጠቀምበት የጨረታ ማስታወቂያ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ብቻ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከቀረቡት ማስረጃዎች ለመረዳት ተችሏል፡፡

56. ለማስታወቂያው ስራ አዲስ ዘመን ጋዜጣን ብቻ ለምን እንደሚጠቀሙ የመ/ቤቱ ኃላፊዎች በኦዲት ቡድኑ ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ፣ ሌሎች ተጨማሪ መንገዶችን ለመጠቀም የራሱ በጀት ስለሚያስፈልገው የአዋጪነት ጥናት በመስራት ጥቅሙ ካመዘነ እንደሚሄዱበት ገልጸዋል፡፡

57. ይሁንና የተሻለ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች እንዳይገኙ ፣ በዚህም ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ እንዲያንስ ፣ የተሻለ ዋጋ የሚያቀርቡ እንዳይሳተፉና ከመረጃ እጥረት የተነሳ ጨረታውን ለመሳተፍ የሚችሉ እድል እንዳያገኙ ስለሚያደርግ፣ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ሁልጊዜ የሚጠቀምበት የጨረታ ማስታወቂያ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ብቻ መሆኑ ተገቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

ተጫራቾች ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ከመጫረታቸው በፊት የቀረበውን የጨረታ ሰነድ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የሚያገናዝቡበት በቂ ጊዜ መሰጠቱን በተመለከተ፤

58. ተጫራቾች ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ከመጫረታቸው በፊት የቀረበውን የጨረታ ሰነድ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የሚያገናዝቡበት በቂ የጉብኝት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

59. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት በኦዲት ቡድኑ በተደረገው የሰነድ ክለሳ ተጫራቾች ለጨረታ የቀረቡ ተሽከርካሪዎችንና ንብረቶችን ነባራዊ ሁኔታ ከገዙት የጨረታ ሰነድ ማስረጃ ጋር ለማገናዘብ የሚሰጠው ቀን ምን ያህል እንደሆነ የተገለጸበት ማስረጃ አልተገኘም፡፡

60. ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በተደረገው ጨረታ ላይ የኦዲት ቡድኑ በመገኘት አገልግሎቱ ጨረታ ካወጣ በኃላ የሚጫረቱትን ንብረትም ሆነ ተሽከርካሪ አጠቃላይ ሁኔታ ለማየት የተሰጠው ጊዜ በቂ ስለመሆኑ ባቀረበው መጠይቅ መሰረት ከ75 ተጫራጮች ውስጥ 13ቱ ጊዜው በቂ አለመሆኑንና ባለመሆኑም የገጠማቸውን ሁኔታ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

- ንብረቶቹን ለማየት ሲኬድ የሚያሳይ ሰው ባለመኖሩ መጉላላት እንዳለና ባለሙያዎቹ /መካኒኮቹ/ ለሚፈልጉት ሰው ብቻ በደንብ እንደሚያሳዩ፣
- የሚሰጠው ቀን በቂ ባለመሆኑ የንብረቶችን ትክክለኛ ምንነት ማወቅ አዳጋች መሆኑን፣
- ከጊዜው እጥረት የተነሳ ከከተማ ውጭ /ክፍለ ሀገር/ ያሉትን መኪኖች ማየት አለመቻል፣
- ንብረቱ በተለያየ ቦታ የተቀመጠ ስለሆነ የጊዜው ማጠር በደንብ ለማየትና ስለንብረቱ ግንዛቤ ማግኘት አለመቻሉን፣
- በቂ ያለመሆኑ ከጊዜ አንፃር ሳይሆን የመኪኖቹን ውስጣዊ ይዞታ በደንብ ለማየት የተወሰኑ መኪኖች ተቆልፈው እንደነበር፣
- የመኪናውን የሞተር ክፍል ቁልፍ የለም ተብሎ ማየት አለመቻል፣
- ከጊዜው እጥረት የተነሳ ከከተማ ውጭ /ክፍለ ሀገር/ ያሉትን መኪኖች ለማየት አለመቻል፣
- የተሰጠው ጊዜ በቂ አለመሆኑን፣ ለምሳሌ የአንዳቸው የጨረታ ቦታ አጋርፋ እንደነበር፣ እዚያ ለማየት በሄዱበት ወቅት መንገዱ በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ ለማየት ጊዜው እንዳልበቃ፣
- መንገዱ ለትራንስፖርት የማይመች በመሆኑና የተሰጠውም ጊዜ አምስት ቀን ብቻ ስለሆነ የተለያዩ ቦታዎች ያሉትን መኪኖች ለማየት አለመቻልና በየክፍለሀገሩ ያሉትን መኪኖች ለማየት ሰፋ ያለ ጊዜ ያልተሰጠው መሆኑን፣
- አንደኛ ንብረቶቹን ለማየት ሲኬድ የሚያሳይ ሰው ማጣት፣ ሁለተኛ ለማየት አይፈቀድም በማለት መጉላላት መኖሩን፣
- የጊዜ ችግር ላለበት ሰው የሚሰጠው ጊዜ በቂ አለመሆኑን፣

- ገጠር አካባቢ (አጋርፋ ግብርና) ሄዶ ለማየት ጊዜው በጣም አጭር በመሆኑ መንግሥት የተሻለ ገቢ ሊያገኝ የሚችለው ጊዜ ቢራዘምና ብዙ ተሳታፊዎች ቢኖሩ መሆኑን፣
- ለማየት የሚሰጠው ቀን ከ15 እስከ 20 ቀን ቢሰጥ ጥሩ እንደሚሆን፣

61. በመሆኑም አገልግሎቱ ለጨረታ ተሳታፊዎች ሁኔታዎችን ያገናዘበ በቂ የጉብኝት ጊዜ አለመስጠቱ ተጫራቾች ስለሚጫረቱበት ንብረት የተሟላ ግንዛቤ እንዳይኖራቸው እና በእውቀት ላይ የተመሰረተ የጨረታ ዋጋ እንዳያቀርቡ ያደርጋል፡፡

የጨረታ አሸናፊ ንብረት ሲረከብ በጨረታ ሰነዱ ላይ በቀረበው ዝርዝር መሰረት መሆኑን በተመለከተ፤

62. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎችን ወቅታዊነትና ትክክለኛነት ሰነዱ ለጨረታ ከመቅረቡ በፊት ሊያረጋግጥና ለአሸናፊውም ተጫራች በሰነዱ መሰረት ርክክብ ሊደረግለት ይገባል፡፡
63. በመሆኑም የኦዲት ቡድኑ በጉዳዩ ላይ ባደረገው የሰነድ ክለሳ የሚከተሉት ተስተውለዋል፤
    - ባለንብረት መ/ቤቱ የሚልከው የተሽከርካሪ መረጃና በአካል የሚገኘው መረጃ መለያየት፣ /የ2005 ዓ.ም. ዓመታዊ የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርት/
    - በሥራ ሂደቱ ባለሙያዎች የታዩ ድክመቶች ከፌዴራል መ/ቤቶች የሚመጡትን የሚወገዱ ተሽከርካሪዎች እና ሌሎች ዕቃዎች ዝርዝር በየጊዜው መረጃውን ወቅታዊ አለማድረግና የመረጃውን ፎቶ ኮፒ አለመያዝ፣ /የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ስለማካሄድ ገጽ 2/
    - በተሽከርካሪ መረጃ አሰባሰብ ላይ የሞተርና የሻንሲ ቁጥር ከመኪና ከፍቶ አለማየት ከሊብሬ ብቻ መረጃ ሰብስቦ መምጣት፣ /የ2004 እና የ2005 የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት/
64. ይህንኑ ጉዳይ ለማጣራት በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በተከናወነው ጨረታ የኦዲት ቡድኑ ተገኝቶ በመጠይቅ ባሰባሰበው ማስረጃ መሰረት ተሽከርካሪ በጨረታ አሸንፌ አውቃለሁ ካሉ 23 መልስ ሰጭዎች ውስጥ የተሽከርካሪ ርክክብ ሲደረግ

የንብረት መጉደል አጋጥሞኛል ያሉ 5ቱ ስለጎደለው ንብረት እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

- መኪናዎችን ማሽነፋችን ከተነገረ በኂላ መኪና ላይ የነበሩት ተንዳኝ ነገሮች ተፈታትተው ገጥሞኛል፡፡ ጥበቃው ቢጠናከር ጥሩ ነው፡፡
- አጋርፋ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ላይ መኪናውን ልመለከት ስሄድ የነበረው ለዚያውም ፎቶ ግራፍ አንስቼ የሄድኩት ዕቃ መኪናውን አሸንፌ ለመውሰድ በሄድኩበት ወቅት ዕቃው ተፈትቶ አግኝቼዋለሁ፡፡ ዕቃዎቹም ሞተሪኖ እና የፊት መብራቶች ናቸው፣
- ንብረትነቱ የሀዋሳ ዩኒቨርሲቲ መኪና ከጨረታው በፊት የነበረውን የመኪና አካል የሀይድሮሊክ ቦለጃውን ተወስዶ አግኝቻለሁ፣
- በፍልውሃ ግቢ ውስጥ የመኪና ጨረታ አሸንፌ ነበር፡፡ ነገር ግን መኪናውን መጀመሪያ ሳየው የጎደለ የለውም፡፡ በኂላ ግን ሞተሪኖ፣ የዘይት ክዳን፣ የማርሽ ቀንድ ተሰርቆ አገኘሁት፡፡
- እንዲሁም ሌላው ተጫራች ጨረታ ካሸነፉ በኂላ ብዙ የጎደሉ ዕቃዎች የጎደሉ መሆኑን ለምሳሌ ሞተሪኖ፣ ዲናሞ እና ኢቫንስ ገልጸዋል፡፡

65. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለአገልግሎት መ/ቤቱ የበላይ ሥራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ ጉዳዩ ትክክል መሆኑንና ንብረትም ሆነ ተሽከርካሪ የሚጎልበት ሁኔታ መኖሩን ይህንን ጉዳይ መ/ቤቶችን ጠርቶ በማነጋገር በቀጣይ እንደሚሰሩበት ገልጸዋል፡፡

66. በመሆኑም የጨረታ አሸናፊዎች የጎደለ ንብረት ሲረከቡ ቅሬታ እንዲያድርባቸው ፣ አገልግሎቱም በቀጣይ ለሚሸጣቸው ንብረቶች በተጫራቾች ዘንድ አመኔታን እንዲያጣ ሊያደርግ እንዲሁም ርክክቡ ወቅታዊ አለመሆኑ በጨረታ አሸናፊዎችን ለእንግልት እና ላላስፈላጊ ወጪ ይዳርጋል፡፡

<u>የጨረታ አሸናፊ የሆነ ባለሀብት የሚጠበቅበትን ክፍያ ከፈጸመ በኃላ የሚደረገው የንብረት ርክክብ ወቅታዊ መሆኑን በተመለከተ፤</u>

67. የሚወገዱ ንብረቶችን ተጫርቶ ያሸነፈ ተጫራች ያሸነፈውን ንብረት በወቅቱ እንዲረከብ አገልግሎቱ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡

68. በመሆኑም የኦዲት ቡድኑ ንብረቶችን በጨረታ የገዙ ባለሀብቶች ክፍያቸውን ከፈጸሙ በኋላ ንብረታቸውን በወቅቱ ስለመረከባቸው ባደረገው የሰነድ ክለሳ የሚከተሉት ተገኝተዋል፡፡

- የገቢዎችና ጉሙሩክ ባለስልጣን እና የአዲስ አበባ መንገድና ትራንስፖርት ቢሮ በጨረታ ለሚወገዱ የተለያዩ ተሽከርካሪዎች በጨረታው አሸናፊ ለሆኑት ተጫራቾች ዜሮ ዲክላራስዮን በወቅቱ አለመስጠትና የስም ዝውውር ላይ አስፈላጊውን የሥራ ትብብር አለማድረግ፣
- አገልግሎቱ ከቤተመንግሥት የተወገዱ ተሽከርካሪዎች ለተፈጠረው የሞተር እና ሻንሲ ቁጥር ስህተት ለማስተካከል ለ8 ደንበኞች ተገቢውን ማስተካከያ እንዲያገኙ በአዲስ አበባ ትራንስፖርት ጽ/ቤት በኩል ለተለያዩ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ደብዳቤ እንዲፃፍላቸው ማድረጉ፣
- ግንቦት 25 እና 26/2004 ዓ.ም. የትራንስፖርት ባሥልጣን ተሽከርካሪዎች ለመሸጥ በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ባወጣው ጨረታ ላይ ተሳትፈው አሸናፊ የሆኑት አቶ ሙላት መኮንን የሠሌዳ ቁጥሩ 4-25270አአ ፣ ሞዴሉ ዋዝ-469 ፣ የሞተር ቁጥሩ 208088፣ የሻንሲ ጠጥሩ 200651 የሆነ ተሽከርካሪ ዋዝ በብር 17325.00 /አሥራ ሰባት ሺህ ሦስት መቶ ሃያ አምስት ብር/ በመክፈል ተሽከርካሪውን መረከባቸውን፣ ሆኖም ባለጉዳዩ የስም ዝውውር ለመፈፀም ሲሄዱ የተሽከርካሪው ዶክመንት ባለመሟላቱ ምክንያት ከአሥር ወር በላይ ምንም አይነት አገልግሎት ያላገኙ መሆኑን ሚያዚያ 8 ቀን 2005 ዓ.ም. ለአገልግሎቱ ከጻፉት ማመልከቻ ለመረዳት ተችሏል፡፡
- አቶ ደረጀ ተክሌ ያሸነፉበት የመለያ ቁጥር 055 የሞተር ቁጥር 27113917 እና የሻንሲ ቁጥር 80110083738 የሆነ ተሽከርካሪ ያሻነፉ መሆናቸውን ከጨረታ ቃለ ጉባኤ ቁጥር 03/2003 ለማረጋገጥ መቻሉን፣ ነገር ግን አሸናፊ የሆኑት ተጫራች ከላይ የተጠቀሰው ተሽከርካሪ መረጃው ለአገልግሎታችን ሲላክ የሞተር ቁጥር የተመታ መሆኑን በግልጽ በተላከው ቅጽ መሠረት ተሞለቶ ባለመቅረቡ በአፈጻጸም ላይ ችግር መፍጠሩና የስም ዝውውር ለማድረግ ከአንድ ዓመት በላይ ስለመጉላላታቸው፣
- በጨረታ ተወዳድረው አሸናፊ የሆኑ አቶ ኢብራሂም ፈጠነ የስም ዝውውር ማድረግ አለመቻላቸውን በመግለጽ ህዳር 17 ቀን 2005 ለአገልግሎቱ

በማመልከታቸው ለመንገድና ትራንስፖርት ቢሮ ትብብር እንዲደረግላቸው ስለመጻፉ፣

- በጨረታ ከተወገዱ ተሽከርካሪዎች መካከል የሠሌዳ ቁጥሩ 35 ዕድ. 1895 የሆነ ተሽከርካሪ አቶ ደምሴ ታደሰ ብላታ አሸናፊ መሆናቸውን በመግለጽ ቃለጉባኤ ለፍትህ ሚኒስቴር ቢላክም የሰሌዳ ቁጥሩ ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ባለመተላለፉ አሸናፊው ተጫራች የስም ዝውውር ለማድረግ የተቸገሩ ስለመሆኑ ያገለገሉ ተሽከርካሪዎች እና ልዩ ልዩ ዕቃዎችን በጨረታ ተወዳድረው አሸናፊ ለሆኑ ሰዎች ከተዘጋጀ ደብዳቤ መገኘቱ፤

69. በተጨማሪም ንብረትነታቸው የውሀ፣ መስኖና ኢነርጂ ሚ/ር የሆኑና በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የተወገዱ 35 መኪኖች ጨረታውን ላሸነፉ ባለንብረቶች በወቅቱ ርክክብ ስለመፈጸሙ የኦዲት ቡድኑ ለሚ/ር መ/ቤቱ የግዢ የፋይናንስና ንብረት አስተዳደር ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ላቀረበላቸው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ፣ መሟላት የሚገባቸው መረጃዎች ስላልተሟሉ አንዳንዶቹን ተሽከርካሪዎች ለተጫራቾች ለማስረከብ እስከ 8 ወር ጊዜ ፈጅቶ እንደነበር ገልጸዋል፡፡

70. በመሆኑም በጨረታ የሚወገዱ ንብረቶችን መሟላት የሚገባውን መረጃ ሳያሟሉ ለጨረታ ማቅረቡ ርክክቡን ለማስፈጸም በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ላይ ጫና የሚፈጥርና ግለሰቦችንም ለእንግልት የሚዳርግ ስለሆነ አሰራሩ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች በጨረታ ያስያዙት ገንዘብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተመላሽ መደረጉን በተመለከተ፤</u>

71. በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች ለጨረታው ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ሰነድ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተመላሽ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

72. የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁ.9/2003 አንቀጽ 25 ንዑስ አንቀጽ 2 ሠ አሸናፊው ተጫራች እንደተመረጠ ወዲያውኑ ጨረታውን ላላሸነፉ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያው ሰነድ መመለስ እንዳለበት ፣ እንዲሁም

አገልግሎቱ በያዘው እቅድ ጨረታውን ለመገምገም የሚወስደው ጊዜ 7 ቀን መሆኑን አስቀምጧል፡፡

73. ይሁንና በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በተከናወነው ጨረታ የኦዲት ቡድኑ ተገኝቶ በመጠይቅ ባሰባሰበው ማስረጃ መሰረት የተሸናፊ ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ሰነድ (C.P.O) እስከ ሀያ ቀን የሚቆይ መሆኑንና ይህም ተጫራጮች ገንዘቡን ለስራ የሚፈልጉት በመሆኑ ቶሎ አለመለቀቁ ቅሬታ የፈጠረባቸው መሆኑን በጽሁፍ አስቀምጠዋል፡፡

74. ስለጉዳዩ የኦዲት ቡድኑ ለአገልግሎት መ/ቤቱ የበላይ ሥራ ኃላፊዎች ላቀረበው ቃለ-መጠይቅ በሰጡት መልስ አንዳንዴ የጨረታ ሰነዶችን ለመገምገም ከሌሎች ስራዎች ጋር ተደርቦ ረጅም ጊዜ እንደሚወስድና ይህ አሰራር ግን እንደሚሻሻል፣ ለጨረታ ሰነድ ግምገማውም በስትራቴጂክ ከተቀመጠው ጊዜ በታች አድርጎ ማስቀመጥና መስራት እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡

75. የጨረታ ማስከበሪያውን ሰነድ (C.P.O) በወቅቱ አለመመለሱ ለተገልጋዮች መንገላታት እንደምክንያት ከመሆኑም በላይ ቅሬታ እየተፈጠረ በሄደ ቁጥር የመ/ቤቱን መልካም ገጽታ ሊያበላሸው ስለሚችል አሰራሩ ትክክል ሆኖ አልተገኘም፡፡

<u>የአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ ሂደት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ መሆኑን በተመለከተ፤</u>

76. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከማችተው የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችንና ተሽከርካሪዎችን የሚያስወግድበት ሂደት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡

77. በኦዲቱ ወቅት እንደታየው የሚወገዱ ንብረቶችን የተሟላ መረጃ ለማጠናቀር ፣ ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ ለማዘጋጀት ፣ ለመ/ቤቶች በመረጃ አያያዝና በንብረት አወጋገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ለመስጠት ፣ ከተገልጋዮች/ባለድርሻ አካላት/ ጋር የመረጃ ልውውጥ ለማድረግ ፣ በስራ አፈጻጸም ወቅት የተገኙ ጠንካራና ደካማ ተሞክሮዎችን ሰብስቦ በመረጃነት ለመጠበቅና ለማስተላለፍ ፣ በአጠቃላይ

የአወጋገድ ስርዓቱ ጥራቱን የጠበቀ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ ለማድረግ አሰራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ አይደለም።

78. በተጨማሪም የሥራ ሂደቱ ንብረት የማስወገድ ስራውን ዘመናዊ ለማድረግ ቴክኖሎጂ መጠቀም አስፈላጊ ነው የሚል እምነት ቢኖረውም ለዚሁ የሚያስፈልግ ቴክኖሎጂ በወቅቱ አለመገንባቱን እንደ ስጋት መውሰዱን በስትራቴጂክ እቅዱ ያስቀመጠ መሆኑን ለማየት ተችሏል።

79. የአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ኃላፊዎች ስለጉዳዩ ተጠይቀው በሰጡት መልስ፣ የአይ ቲ ዲፓርትመንት ሶፍትዌር ዴቨሎፕ አድርጎ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

80. ይሁን እንጂ ሶፍትዌር ዴቨሎፕ የማድረጉ ሥራ በምን ደረጃ እንዳለ እና መቼ ተጠናቆ ወደ ሥራ እንደሚገባ የተሟላ መረጃ እና ማስረጃ አልቀረበም።

81. በመሆኑም አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የሚሰራው የማስወገድ ስራ አገር አቀፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አፈጻጸሙ ቅልጥፍናን የሚጠይቅ በመሆኑ ስራውን ፈጣንና ተደራሽ ከማድረግ አንጻር የጎላ ሚና እንዳይኖረው ስለሚያደርግ አሰራሩ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ አለመታገዙ ትክክል ሆኖ አልተገኘም።

<u>አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ንብረት ለሚያስወግድላቸው ባለድርሻዎች መደበኛ እና ተከታታይ የግንዛቤ ማስጨበጫ መስጠቱን በተመለከተ፤</u>

82. አገልግሎቱ ንብረት ከሚወገድላቸው የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ አያያዝ እና አወጋገድ ዙሪያ ውይይት የሚደረግበት መደበኛ እና ተከታታይ የግንዛቤ መፍጠሪያ መድረክ ሊያዘጋጅ እና በውይይቱ ለሚነሱ ጉዳዮች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል።

83. ሆኖም በኦዲቱ ወቅት የኦዲት ቡድኑ በጉዳዩ ላይ ባደረገው የሰነድ ክለሳ፡-

- በፌዴራል መስሪያ ቤቶች ያለአገልግሎት ተከማችተው የሚገኙ ልዩ ልዩ ንብረቶችና ተሽከርካሪዎች በብዛት ቢገኙም የባለንብረት መስሪያ ቤቶች ስለንብረት ማስወገድ ያላቸው ግንዛቤ በእጅጉ አናሳ በመሆኑ ንብረቶችን አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ይዘው እንደሚገኙና ይህ ደግሞ ለሥራ ሂደቱ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ተጽዕኖ የሚያሳድር ስለሆነ ለሚመለከተው ሁሉ

ግንዛቤ እንዲጨብጡ ቢደረግ የተሻለ ውጤት ሊገኝ እንደሚችል፣

- የሚወገዱ ንብረቶች መረጃና ጥናት የሥራ ሂደት በ13 የፌዴራል መ/ቤቶች ላይ በንብረት አያያዝ ፣ አጠቃቀምና አወጋገድ ላይ የተስተዋሉትን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ዝርዝር ለማኔጀመንቱ ሲያቀርብ አንዱ ግኝት የግንዛቤ ችግር መሆኑ፣
- የፌዴራል መ/ቤቶች ፣ አገልግሎቱ እና ባለድርሻ አካላት ተቀራርበው አለመስራታቸው የማስወገድ ሂደቱን ቀልጣፋ እንዳይሆን ማድረጉ፣

84. አገልግሎቱ ከመ/ቤቶች በቀረበ ጥያቄ መሰረት በአካል በመገኘት ፣ በደብዳቤ ፣ በስልክ እና በስልጠና ለመ/ቤቶች በመረጃ አያያዝና በንብረት አወጋገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ እንደሚሰጥ በእቅዱ ማስቀመጡንና በተያዘው እቅድ መሰረት ኦዲቱ በሸፈነው ጊዜ ውስጥ (2004-2006በ.ዓ) የ160 መ/ቤት ጉዳዩ የሚመለከታቸው ኃላፊዎች በአካል አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በመምጣት ፣ ለ42 መ/ቤቶች በስልክ ፣ ለ4 መ/ቤቶች በደብዳቤ ለ5 መ/ቤቶች በስልጠና ሙያዊ ድጋፍ መሰጠቱን የሚያሳይ ማስረጃ ቀርቧል፡፡

85. ሆኖም በናሙና በተመረጡ መ/ቤቶች በንብረት አያያዝና አወጋገድ ዙሪያ ምን ያህሉ ግንዛቤውን እንዳገኙ ለማወቅ በቀረበ ቃለ-መጠይቅ፣ በናሙና በታዩ ሁሉም መ/ቤቶች በስራው ላይ የሚገኙ ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው ሰራተኞች አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ባዘጋጀው ስልጠና ተሳትፈው እንደማያውቁ ገልጸዋል፡፡

86. የገንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ለምን እንደማይዘጋጁ የኦዲት ቡድኑ ለመ/ቤቱ ኃላፊዎች በቃለመጠይቅ ላቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት መልስ ግንዛቤውን ሁሉም መ/ቤቶች በተገኙበት መሰጠቱና ይህንኑ የሚያስረዳ ማስረጃ መኖሩን ገልጸዋል፡፡

87. ይሁንና የቀረበው ማስረጃ የሚያሳየው ኦዲቱ በሸፈነው ጊዜ ውስጥ (ከ2004 - 2006 በ.ዓ.) አንድ ጊዜ ብቻ (ጥር 29/2006 ዓ.ም) ከፌደራል ባለበጀት መስሪያ ቤቶችና አቅራቢ ድርጅቶች ጋር ለመመካከር ያዘጋጀው የምክክር መድረክ እንደነበረና በመድረኩም በ2004 ፣ 2005 እና የ2006 ግማሽ ዓመት

በአገልግሎቱ የተፈጸሙ ግዥዎችንና የተወገዱ ንብረቶችን የሚመለከት ፅሁፍ ማቅረቡን የሚገልጽ ነው፡፡

88. በመሆኑም የስልጠናውን ጊዜ በእቅድ በመያዝ ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው የስራ ኃላፊዎች ተያያዥና ተከታታይ ስልጠና በመስጠት ያለውን የእውቀት ክፍተት ለማጥበብና አቅማቸውን ማጎልበት እንዳይችል አድርጎታል፡፡

ክፍል ሦስት

የመደምደሚያ ሃሳቦች

89. በጨረታ የተሸጡ የመንግስት መ/ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የንብረት አወጋገድን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የተደረጉ ጥረቶች እንደተጠበቁ ሆነው ፤ ከክዋኔ ኦዲት ዋና ዋና ዓላማዎች አንዱ በመንግስት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ተፈፃሚና ውጤታማ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ከዚህ ዓላማ አንፃር ንብረት አወጋገድ ሂደቱን ቀልጣፋ እና ውጤታማነት በሚከተሉት ምክንያቶች አጥጋቢ ሆኖ አልተገኘም፡፡

89.1 በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ር የተዘጋጀው የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ተፈጻሚነት የሚያዳግቱ ናቸው ይሻሻሉ ተብለው በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የቀረቡ የማሻሻያ ሀሳቦች በመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ወቅታዊ መልስ አለማግኘታቸው፣

89.2 አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በየዓመቱ የምን ያህል መ/ቤቶችን ፣ ስንት ተሽከርካሪና ንብረት እንደሚያስወግድ በስትራቴጂክ እቅዱ (2002-2007) ዓ·ም አለማስቀመጡ፣

89.3 በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በያዘው እቅድ መሰረት ከመ/ቤቶች የሚወገድ ንብረት መረጃ ለመሰብሰብ ቅጾችን አለመላኩና፣ ለተላከላቸውም መ/ቤቶች መረጃውን እንዲልኩ የሚያደርገው ክትትል ስልክ ብቻ መሆኑ፣

89.4 በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከማችተው የሚገኙና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች ቢኖሩም በወቅቱ እንዳይወገዱ ምክንያት የሆኑ የሚከተሉት ኃሳቦች መኖራቸው፤

- በመመሪያ ቁ.9/2003 የማስወገጃ ጊዜ ገደብ አለመኖር፣
- በመስሪያ ቤቶች ለዘመናት ተከማችተው የሚገኙ ንብረቶች እንዲወገዱ በወቅቱ ውሳኔ አለመስጠት፣
- ንብረት እንዲወገድላቸው የሚጠይቁ የፌዴራል መስሪያ ቤቶች የሚልኩት መረጃ የተሟላና ትክክለኛ አለመሆን፣

- በፌዴራል መስሪያ ቤቶች ለሚወገዱ ንብረቶች አያያዝ የሚሰጠው ትኩረት አናሳ መሆን፣
- ለስራው ተገቢው ባለሙያ የማይመደብበትና ፣ ተቋማዊ ትኩረት ያልተሰጠው መሆኑ፣
- ቦታው ላይ የሚመደቡ ባለሙያዎች የስራ ፍልሰት መኖሩና ለስራው አዲስ የሆኑ ሰራተኞች ቦታው ላይ መገኘታቸው፣
- ስራው በቀጥታ የሚመለከታቸው ሰራተኞች በንብረት አያያዝና አወጋገድ ላይ ተከታታይ ስልጠና አለማግኘታቸው፣
- አብዛኛዎቹ የመንግስት መ/ቤቶችና የልማት ድርጅቶች ኃላፊዎች በንብረት አስተዳደር ስለሚሰሩ ስራዎች ተገቢውን ትኩረት የማይሠጡና መረጃዎች የሌላቸው መሆኑ፣
- የማስወገዱን ስራ ለመስራት የሚዋቀሩት ኮሚቴዎች ንብረቱ በቀጣይ እንደማያገለግል እርግጠኛ መሆን ፣ ንብረቶችን በየአይነታቸው መለየትና ዋጋ ማውጣት ስለሚጠበቅባቸው፣ ንብረቶቹ የቆዩ ከመሆናቸው የተነሳ ስራው አድካሚና ጤንነትን ስጋት ላይ የሚጥል በመሆኑና ከመደበኛ ስራቸው ጋር ደርበው የሚሰሩትና ምንም የማበረታቻ ክፍያ የሌለው በመሆኑ አወጋገዱን እንዲዘገይ ማድረጉ፣
- ከየመስሪያ ቤቶች ኮምፒውተሮችንና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን እንዲያስወግድ ስልጣን የተሰጠው የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር ንብረቶቹን ለማንሳት አቅሙ ገና መሆኑ፣
- የንብረት ገቢ ደረሰኝ ሳይቆረጥላቸው ገቢ የሚደረጉ ንብረቶች መኖራቸው፣
- የሚወገዱ ንብረቶች ቶሎ ባለመወገዳቸው ለአያያዝና አጠባበቅ ሰራተኞች ላይ የስራ ጫና መፍጠራቸው፣
- በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ንብረቶችን በአፋጣኝ ለማስወገድ በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል ይዞ አለመንቀሳቀሱ፣
- የሚወገዱ ንብረቶችን ዋጋ ለማውጣት የሚያስችል ቀመር አለመኖሩ፣

89.5 አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ከሚያወጣው ጨረታ ጋር ተያይዞ፤

- የመ/ቤቶችን ንብረትና ተሽከርካሪ ለማስወድ የሚጠቀምበት የጨረታ ማስታወቂያ ጥሪ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ብቻ መሆኑ፣

- አንዳንድ ተጫራቾች የሚጫረቱትን ንብረት ለማየት የሚሰጠው ጊዜ በቂ አለመሆኑን መግለጻቸው፣
- አንዳንድ በጨረታ ያሸነፉ ግለሰቦች ንብረቱን ሲረከቡ በፊት ካዩት የጎደሉ ንብረቶችን ማግኘታቸው፣
- አንዳንድ በጨረታ ያሸነፉ ግለሰቦች ያሸነፉትን ንብረቶች ክፍያ ፈጽመው ለመረከብ ሲሄዱ የንብረቱ መረጃ ያልተሟላ በመሆኑ እስከ አንድ አመት መዘግየቱ፣
- አንዳንድ በጨረታ የተሸነፉ ግለሰቦች ያስያዙት የጨረታ ማስከበሪያ ሰነድ (C.P.O) በወቅቱ ባለመመለሱ ቅሬታቸውን መግለጻቸው፣

89.6 አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የሚሰራውን የማስወገድ ስራ ጥራቱን የጠበቀ፣ ቀልጣፋና ተደራሽ የሚያደርግለትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ የማይጠቀም መሆኑ፣

89.7 አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት በባለንብረት መስሪያ ቤቶች በሚገኙ ባለሙያዎች ስለንብረት ማስወገድ ያለውን የግንዛቤ እጥረት ለመቅረፍ መደበኛና ተከታታይ ስልጠና አለመስጠቱና ይህንኑም ለማድረግ የሚያስችል እቅድ አለመያዙ፣

በአጠቃላይ በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን የአሰራር ግድፈቶች ሊያርሙና አገልግሎቱን ከሚጠበቅበት አገራዊ ተልእኮ አንጻር የተሻለ አሰራር እንዲኖረው ያስችላሉ ተብለው የታመነባቸው የሚከተሉት የማሻሻያ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ክፍል አራት

የማሻሻያ ኃሳቦች

የሰነድ ክለሳን በተመለከተ የመንግስት ግዢና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የፌዴራል መንግስት ንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003ን በሚመለከት ከአገልግሎት ሰጪውና ከሌሎች የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ያሰባሰበውን ግብዓት በመጠቀም መመሪያውን ለማሻሻል የጀመረው የክለሳ ስራ ቢፋጠን በአፈጻጸም የሚፈጠረውን ክፍተት ስለሚሸፍን አፈጻጸሙ ላይ ትኩረት ሊሰጠውና አገልግሎቱም ለአፈጻጸሙ ክትትል በማድረግ የድርሻውን ሊወጣ ይገባል፡፡

- ✓ የመረጃ አሰባሰብን በተመለተ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት ከሚሰጣቸው መ/ቤቶች መረጃዎችን በመሰብሰብ በስትራቴጂክ እቅዱ ሊያካትታቸውና በየበጀት አመቱ ባስቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለማከናወኑ አፈጻጸሙን ሊለካ ይገባል፡፡
- ✓ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተከማችተው የሚገኙና አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች በወቅቱ እንዲወገዱ ሊደረግ ይገባል፣
- ✓ ንብረቶችን በአግባቡ የመረከብ ፣ የመያዝ ፣ ለተገቢው ስራ የመጠቀምና የአገልግሎት ጊዚያቸው ሲያበቃ የማስወገድ ተግባር ትልቅ ተቋማዊ ትኩረት የሚያስፈልገው በመሆኑ የተቋማት ኃላፊዎች ቦታው ላይ የሚመደቡ ሰራተኞችን የስራ ብቃት ሊለኩና በቂ የትምህርት ዝግጅት እና የስራ ልምድ ባለው የሰው ኃይል ሊያደራጁትና ቦታው ላይ ስለሚሰራው ስራ የሚቀርቡ ሪፖርቶችን አጽንኦት ሰጥተው ሊከታተሉ፣
- ✓ በስጦታም ሆነ በግዢ የተገኙ ንብረቶችን በአግባቡ የመረከብ ፣ የመያዝ፣ ለተገቢው ስራ የመጠቀምና የአገልግሎት ጊዜው ሲያበቃ ማስወገድ እንዲቻል ቋሚ ንብረቶች ሲገቡም ሆነ ሲወጡ ገቢና ወጪ ደረሰኝ ሊኖራቸው፣
- ✓ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚ/ርም መ/ቤቶች የሚወገድ ንብረት መኖሩን ሲያረጋግጡ አፋጣኝ እርምጃ እንዲወስዱ የሚያስችል አስገዳጅ የጊዜ ገደብ ሊያበጅ፣

- ✓ ኮምፒውተሮችንና የኤሌክትሮኒክስ እቃዎችን እንዲያስወግድ ስልጣን የተሰጠው የመገናኛኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚ/ር አቅሙን የማሳደግ ስራውን በማፋጠን የተሰጠውን ኃላፊነት ሊወጣ፣
- ✓ አገልግሎት ሰጪውም ቀመር ሊዘጋጅላቸው የሚችሉ ንብረቶችን ለይቶ ቀመር በመስራት በየጊዜው የመተኪያ ዋጋ ጥናት ለማድረግ የሚወስደውን ጊዜና ወጪ ለመቀነስና ወጥ አሰራርን ሊያሰፍን ይገባል፣
- ✓ በማስወገዱ ስራ ላይ የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ተከታታይነት ያለው ስልጠና ጉዳዩ በቀጥታ ለሚመለከታቸው ሰራተኞች ሊሰጥ ሊሰጥ፣ ይገባል፡፡ ይህም ሁኔታ ተፈጻሚ ሲሆን የሚወገዱ ንብረቶች ለባሰ ብልሽትና ሥርቆት ሳይጋለጡና ለአካባቢ ብክለትን ሳይፈጥሩ በአፋጣኝ እንዲወገዱ ፣ በዚህም አገሪቱ የጀመረችውን የልማት ስራ ለማፋጠን የሚያስችል ተጨማሪ ገቢ እንዲገኝ ያስችላል፡፡
- ✓ የጨረታ ማስታወቂያ ጥሪን በተመለከተ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የራሱን ድረ-ገጽ ጨምሮ የተለያዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ጥሪ ቢያደርግ በጨረታው የተሻለ ቁጥር ያላቸው ተሳታፊዎች እንዲገኙ ያግዛል፡፡ ይህም ከጨረታ ሰነድ ሽያጭ የሚገኘው ገቢ እንዲያድግ ፣ በተሻለ ዋጋ የሚያቀርቡ ተሳታፊዎች እንዲገኙና ከመረጃ እጥረት የተነሳ እድል ላላገኙ ተጫራቾች እድል ለመስጠት በር የሚከፍት በመሆኑ በጀት ለማስፈቅድ አስቀድሞ የአዋጪነት ጥናት ሊሰራ ይገባል፡፡
- ✓ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት ንብረቶችንም ሆነ ተሽከርካሪዎችን በጨረታ ለመሸጥ ሲፈልግ ጨረታ ሰነዶች ላይ የሚሰፍሩ መረጃዎች ትክክለኛ መሆናቸውን አስቀድሞ ሊያጣራ፣ መረጃቸው ያልተሟላ ንብረቶች ለጨረታ እንዳይቀርቡ ሊያደርግ ፣ ጨረታውን ሲያወጣ ተጫራቾች ንብረቱን ለማየት የሚሰጣቸው ጊዜ በቂ መሆኑን ሊፈትሽና መስተካከል ካለበት ሊያስተካክል ፣ ሲሸጡም የጨረታው አሸናፊዎች በጨረታ ሰነዱ ላይ በተቀመጠው ማስረጃ መሰረት ከባለንብረት መ/ቤቱ በወቅቱ መረከባቸውን ሊያረጋግጥ ፣ የአሰራር ክፍተት ካለ ጣልቃ በመግባት ችግሩ የሚፈታበትን መንገድ ሊያመቻችና የጨረታ ሰነዶችን በወቅቱ በመገምገም

የጨረታ ማስከበሪያ ሰነዶችን ለተሸናፊዎች ሊመልስና በጨረታውም ቀን መቼ ሰነዱ እንደሚመለስ ሊያሳውቅ ይገባል፡፡

- ✓ በየመንግስት መ/ቤቱ የተከማቹና ለከፋ ብልሽት እየተጋለጡ ያሉ ለመ/ቤቶቹም ቦታዎችን በመያዝ ለአያያዝና አጠባበቅ ችግር የፈጠሩና በአፋጣኝ መወገድ የሚገባቸው ንብረቶች በመኖራቸው፣ ሲወገዱም የሚያመጡትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ከግምት በማስገባትና አገልግሎት ሰጪው መ/ቤትም ይህንኑ ስራ ለማፋጠን የሰው ኃይሉን አሟልቶ መንቀሳቀስ ስላለበት ቢሮዎች እስኪገነቡ መጠበቅ ከሚያመጣው አሉታው ተጽዕኖ አንጻር ታይቶ አማራጮችን ማየት የተሻለ ይሆናል፡፡
- ✓ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የሚሰራው የማስወገድ ስራ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ቢታገዝ አገልግሎቱ አገር አቀፍ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አፈጻጸሙን ለማሻሻልና ተደራሽ ለማድረግ የጎላ ሚና ስለሚኖረው ጅምሩን ስራ ማፋጠን ይጠበቅበታል፡፡
- ✓ በናሙና የታየው አዳማ ዩኒቨርስቲ እንደማሳያ ሆኖ በተላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወርክ ሾፖች ቢኖሯቸውና ንብረቶች ለሽያጭ ከሚቀርቡ ይልቅ ቢጠገኑ ወይም በግብዓትነት ቢጠቀሙባቸው ለሰራተኛው የስራ እድል ከመፍጠራቸውም በተጨማሪ የሀገር ሀብትን በአግባቡ መጠቀም ያስችላሉ፡፡

በመጨረሻም ለንብረት ግዢና ማስወገድ አገልግሎት ሠራተኞች በኦዲቱ ወቅት ለኦዲት ቡድኑ የተጠየቁትን መረጃዎች በወቅቱ በማቅረብና ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ በመስጠት ስላደረጉልን ያላሰለሰ የሥራ ትብብር ልባዊ ምስጋናችንን እናቀርባለን፡፡

አባሪ 1

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎችና የመመዘኛ መስፈርቶች

Audit Issues and Evaluative Criterias

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
1. አገልግሎቱ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የንብረት አወጋገድን ለማቀላጠፍ የሚያስችል ጠንካራ የመረጃ ማጠናከሪያና አያያዝ ሥርዓት እንዲሁም ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ አሰራርን ኢኮኖሚያዊ ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ ተግባራዊ ማድረጉን መገምገም፡፡	
1.1. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች የመረጃ አያያዝን በብቃት ለማስተዳደር እና የተሟላ መረጃ ለመያዝ የሚያስችል የአሰራር	1.1.1. አገልግሎቱ በመንግስት ንብረት አወጋገድ ዙሪያ የወጡ አዋጆች፣ ደንቦች እና እነኝህን መሰረት አድርገው የወጡ መመሪያዎች ተግባራዊ ሲደረጉ በአፈጻጸም ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችን በጥናት በመለየት አፈጻጸሙን ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል የማሻሻያ ሃሳብ ለሚመለከተው አካል ሊያቀርብ እና በወቅቱ ተግባራዊ እንዲሆን ሊከታተል ይገባል፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
ሥርዓት የዘረጋ እና ተግባራዊ ያደረገ መሆኑን መገምገም፡፡	1.1.2. አገልግሎቱ በንብረት አወጋገድ ዙሪያ የሚወጡ መመሪያዎች እና ሰርኩላሮች ንብረት ለሚወገድላቸው መ/ቤቶች በወቅቱ እንዲደርሳቸው እና ተግባራዊ መደረጉን ለመከታተል ፣ለመቆጣጠር እና ለመደገፍ የሚያስችለው የአሰራር ስርአት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	1.1.3. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ አገልግሎት በሚሰጣቸው የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተከማቹ እና መወገድ የሚገባቸውን ንብረቶች በመረጃ ቋት /data base/ በመያዝ በየአመቱ የየትኛው መ/ቤት፣ ምን ያህል እና የሚወገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ በስትራቴጂክ እቅድ ሊይዝ ይገባል፡፡
	1.1.4. አገልግሎቱ ስትራቴጂክ እቅዱን መሰረት በማድረግ ከሚወገዱ ንብረቶች ውስጥ በየበጀት አመቱ የየትኛው መ/ቤት ፣ ምን ያህል እና የሚወገዱበትን የጊዜ ሰሌዳ አመታዊ እቅድ ሊያዘጋጅ ይገባል፡፡
	1.1.5. አገልግሎቱ በየበጀት አመቱ ባዘጋጀው እቅድ መሰረት ለማከናወኑ የእቅድ ክንውን ሪፖርት ሊያዘጋጅ እና ክንውኑ ከእቅዱ ካነሰ ምክንያቱን በመለየት በአፈጻጸም ወቅት ላጋጠሙ ችግሮች የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ይገባል፡፡
	1.1.6. በአገልግሎት ሰጪው መ/ቤት አገልግሎት

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
	እንዲያኙ በገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የተዘረዘሩ የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገድ ንብረት እንዳላቸው ለማረጋገጥ በአመት ሁለት ጊዜ የመረጃ ማሰባሰቢያ ቅጽ የመላክና ምላሽ መስጠታቸውን ክትትል የማድረግ ስራ በአገልግሎቱ ሊሰራ ይገባል፡፡
	1.1.7. የሚወገዱ ንብረቶች ሲኖሩ አገልግሎት ሰጪው መ/ቤትና ንብረት የሚወገድለት መ/ቤት ስለሚወገደው ንብረት የጋራ መተማመኛ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
	1.1.8. የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚወገዱ ንብረቶችን ለሌላ አካል በስጦታ ሲያስተላልፍ በስጦታ የተላለፈለት መ/ቤት ወይም ማህበር ሕጋዊ መሆኑ ሊረጋገጥና ርክክብ የተፈጸመበትን ሰነድ አገልግሎቱ በግልባጭ እንዲያውቀው ሊያደረግ ይገባል፣
	1.1.9. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ያስወገዳቸው እና ገና የሚወገዱ የመንግሥት መ/ቤቶች ተሽከርካሪና ንብረት ዝርዝር ማስረጃ ተጠናቅሮ ሊቀመጥ ይገባል፡፡
	1.1.10. አገልግሎቱ በንብረት ማስወገድ ስራው ያጋጠሙትን ጠንካራና ደካማ ጎኖች እየለየ በመረጃነት የሚይዝበት አሰራር ሊኖረውና

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
	የንብረት ማስወገድ ስራው ያስከተለውን አጠቃላይ ውጤት ሊገመግም ይገባል፡፡
	1.1.11. አገልግሎት ሰጪው መ/ቤት የንብረት ማስወገድ አገልግሎቱን ቀልጣፋና ውጤታማ ለማድረግ እንዲችል የክህሎት ክፍተትን መሰረት ያደረገ ስልጠና ያገኘና በመዋቅሩ መሰረት የተሟላ የሰው ኃይል ሊኖረው ይገባል፡፡
1.2. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች ወቅታዊ የመተኪያ ዋጋ አዘገጃጀትና አፈጻጸምን መገምገም፤	1.2. አገልግሎቱ በፌደራል መንግስት መ/ቤቶች ለሚወገዱ ንብረቶች የጨረታ መነሻ ዋጋ እንዲኖር ቀመር ሊዘጋጅላቸው የሚችሉ የንብረት አይነቶችን በጥናት በመለየት ቀመር ሊያዘጋጅላቸውና ቀመር ሊዘጋጅላቸው የማይችሉ ንብረቶችንም ወጥ በሆነ አሰራር እንዲወገዱ ለማድረግ በግልጽ የተቀመጠ የአሰራር መመሪያ ሊኖር ይገባል፡፡
2. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የጨረታ ሂደትና የንብረት አወጋገድ ስርዓት አፈጻጸም ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤	
2.1 **የጨረታ ሂደትን በተመለከተ፤**	2.1.1. በሁሉም የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች ለሚወገዱ ተመሳሳይ ንብረቶች የሚደረገው የንብረት አወጋገድ ሥርዓት ወጥና ግልጽ አሰራርን የተከተለ ሊሆን ይገባል፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
	2.1.2. አገልግሎቱ በፌዴራል የመንግሥት መ/ቤቶች የሚገኙና ያለጥቅም የተቀመጡ ንብረቶችን ለማስወገድ ጨረታ ከማውጣቱ በፊት ስለሚወገዱት ንብረቶች ትክክለኛና የተሟላ መረጃ ሊያጠናቅርና ለጨረታ ሲያቀርብም መረጃውን ወቅታዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	2.1.3. አገልግሎቱ ለሚወገዱ ንብረቶች የሚወጡ ጨረታዎችን ጥሪ የሚያስተላልፍባቸው መንገዶች ተሳታፊዎችን ለመድረስ የሚችል ሰፊ ሽፋን ያለው መሆኑን ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡
	2.1.4. ተጫራቾች ለጨረታ የቀረቡ ንብረቶችን ከመጫረታቸው በፊት የቀረበውን የጨረታ ሰነድ ከነባራዊው ሁኔታ ጋር የሚያገናዝቡበት በቂ የጉብኝት ጊዜ ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
	2.1.5. በጨረታ ሽያጭ ለሚወገዱ ንብረቶች የሚደረገው የጨረታ ሂደት ግልጽነትንና ተጠያቂነትን የሚያጠናክር መሆኑ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡
	2.1.6. አገልግሎቱ የሚወገዱ ንብረቶችን በጨረታ ለመግዛት የተጫረቱ ባለሀብቶችን አሸናፊና ተሸናፊ ሊለይና ከለየም በኃላ ውጤቱን የሚያሳውቅበት መንገድ ግልጽና ተጠያቂነት ያለበት ሊሆን ይገባል፡፡
	2.1.7. የሚወገዱ ንብረቶችን ተጫርቶ ያሸነፈ ባለሀብት የሚጠበቅበትን ክፍያ ፈጽሞ ንብረት የሚረከብበት የጊዜ ሰሌዳ ሊኖርና በተወሰነው ጊዜም

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
	በጨረታ ሰነዱ ላይ በቀረበው ዝርዝር መሰረት ወቅታዊ ርክክብ እንዲደረግለት አገልግሎቱ እገዛ ሊያደርግ ይገባል፡፡
	2.1.8. የሚወገዱ ንብረቶችን በጨረታ ያሸነፈ ተጫራች የሚጠበቅበትን ክፍያ ፈጽሞ ንብረት የሚረከብበት የጊዜ ሰሌዳ ሊኖርና በተወሰነው ጊዜም ክፍያውን ፈጽሞ ንብረቱን ካላነሳ የሚወሰድ እርምጃ ሊቀመጥና አፈጻጸም ሊያገኝ ይገባል፡፡
	2.1.9. አገልግሎቱ ከጨረታ ሽያጭ የተገኘው ገንዘብ በሙሉ መሰብሰቡን እና ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ፈሰስ መደረጉን ማረጋገጥ አለበት፡፡
	2.1.10. በጨረታው ተሸናፊ የሆኑ ተጫራቾች በጨረታ ያስያዙት ገንዘብ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ መሰረት ተመላሽ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡
	2.1.11. አገልግሎቱ ያስወገዳቸውን ንብረቶች በተመለከተ የደንበኞች አቤቱታና ቅሬታ ሲኖር ጉዳዩን አጣርቶ ተገቢውን ምላሽ በወቅቱ ሊሰጥና የቅሬታው ትክክለኛነት ከተረጋገጠ ለወደፊት የተነሱት ችግሮች እንዳይደገሙ እንደግብዓት ሊጠቀምባቸው ይገባል፡፡
2.2. የንብረት አወጋገድ ስርዓት አፈጻጸምን በተመለከተ	2.2.1. አገልግሎቱ በፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የሚገኙ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችን የሚያስወግድበት ሂደት በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ ሊሆን ይገባል፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
	2.2.2. የፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የንብረት ይወገድልኝ ጥያቄ ሲያቀርቡ አገልግሎቱ ንብረቱን የሚያስወግድበት ሂደት የጊዜ ገደብ ሊቀመጥለትና ተግባራዊ ሊሆን ይገባል፡፡
3. አገልግሎቱ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች እና ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በንብረት አወጋገድ ዙሪያ የቅኝጅታዊ አሰራር መድረኮችን በማዘጋጀት አስፈላጊውን ሙያዊ ድጋፍ እያበረከተ ስለመሆኑ መገምገም፤	
3.1 ቅንጅታዊ አሰራርን በተመለከተ፤	3.1.1. አገልግሎቱ ለፌዴራል መንግስት መ/ቤቶችና ለባለድርሻ አካላት ስለሚያከናውነው የንብረት ማስወገድ ስራ ግንዛቤ የሚፈጥርበትን የተለያየ መድረክ ሊያዘጋጅና የማስወገድ ስራውንም በቅንጅት ሊሰራ ይገባል፡፡
	3.1.2. አገልግሎቱ ንብረት ከሚወገድላቸው የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች እና ባለድርሻ አካላት ጋር የሚወገዱ ንብረቶች መረጃ አያያዝ እና አወጋገድ ዙሪያ ውይይት የሚደረግበት መደበኛ እና ተከታታይ መድረክ ሊያዘጋጅ እና በውይይቱ ለሚነሱ ጉዳዮች ወቅታዊ ምላሽ ሊሰጥ ይገባል፡፡

የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫ /Audit Issues/	የኦዲት መስፈርቶች /Evaluative Criteria/
3.2. ሙያዊ ድጋፍ አሰጣጥን በተመለከተ፤	3.2.1 የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የሚወገዱ ንብረቶችን መረጃ በአግባቡ እንዲይዙ አገልግሎቱ ሙያዊ እገዛ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡
	3.2.2 አገልግሎቱ የሚወገዱ ንብረቶችን በተመለከተ ለፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች በንብረት አወጋገድ ዙሪያ ሙያዊ ድጋፍ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡